# - ሀ -

ሀ ሳይሉ ጥፈት ፣ ውል ሳይዙ ሙግት ።

ሀ ባሉ ፣ ተዝካር በሉ ።

ሀሜተኛ ያፍራል ፣ ሀሰተኛ ይረታል ።

ሀምሌ ቢያባራ ቢጋ ይመስላል ።

ሀሰተኛ ቢቃሉ ፣ ስደተኛ በቅሉ ።

ሀሰተኛ ፣ ብርቱ ወንጀለኛ ።

ሀሰተኛን ሲረቱ ፣ በወንድም በእህቱ ።

ሀሰት ስለበዛ ፣ እውነት ሆነ ዋዛ ።

ሀሰት ቢናገሩ ፣ ውቃቢ ይርቃል ።

ሀሰት ነገር ክፉ ፣ ገሀነም እሳት ትርፉ ።

ሀሳቡ ጥልቅ ፣ ነገሩ ጥብቅ ።

ሀሳብ ከውለታ አይቆጠርም ።

ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ ፣ ድሀ ለድሀ ይለቃቀሱ ።

ሀብታም ሲወድቅ ከሰገነት ፣ ድሀ ሲወድቅ ከመሬት ።

ሀብታም በመመፅወቱ ፣ ድሀ በፀሎቱ ።

ሀብታም በከብቱ ፣ ድሀ በጉልበቱ ።

ሀብታም በወርቁ ፣ ድሀ በጨርቁ ።

ሀብታም በገንዘቡ ፣ ድሀ በጥበቡ ፣ እርስ በርስ ይቃረቡ ።

ሀብታም በገንዘቡ ይኮራል ፤ ድሀ በጥበቡ ይከብራል ።

ሀብታም ነው መባል ያኮራል ፤ ድሀ ነው መባል ያሳፍራል ።

ሀብታም እንደሚበላለት ፣ ድሀ እንደሚከናወንለት ።

ሀብታም ያለ ድሀ አይኮራም ፤ ድሀ ያለ ሀብታም አይበላም ።

ሀብታም ገንዘቡን ያስባል ፤ ድሀ ቀኑን ይቆጥራል ።

ሀብትና እውቀት ፣ አይገኝም ባንድነት ።

ሀኪም ሲበዛ በሽተኛው ይሞታል ።

ሀኪም የያዘው ነፍስ ባያድር ይውላል ።

ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ፣ ከቤትሽ አልወጣ ።

ሀይለኛ ውሃ አሻቅቦ ይፈሳል ።

ሁለተኛ ግፌ ፣ ጫንቃዬን ተገርፌ ፣ ልብሴን መገፈፌ ።

ሁለተኛ ጥፋት ፣ ቆሞ ማንቀላፋት ።

ሁለተኛ ጥፋት ፣ ከገበያ ማንቀላፋት ።

ሁለቱን የተመኘ ፣ አንዱንም አላገኘ ።

ሁለት ሆነው የተናገሩት ፣ በመሬት የቀበሩት ።

ሁለት ቁና ሰጥቼ ፣ አንድ ጥንቅል ።

ሁለት ነዶ ይዞ ፣ ወደ ክምር ጠጋ ።

ሁለት አይወዱ ፣ ከመነኮሱ አይወልዱ ።

ሁለት አገር አራሽ ፣ ለባልንጀራው አውራሽ ።

ሁለት እግር አለኝ ብሎ ፣ ከሁለት ዛፍ አይወጡም ።

ሁለት ወፎች ባይናከሱ ፣ ይናቀሱ ።

ሁለት የወደደ ፣ አንዱን ሳያገኝ ሄደ ።

ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም ።

ሁለት ጊዜ ተናግረህ ከፋህ ፣ ሁለት ጊዜ በላህ ተፋህ ።

ሁለት ጊዜ ነው የዶሮ ልደት ፥ አንዱ በእንቁላል አንዱ በሚጨሆት ።

ሁለት ጊዜ ይፈርዱ ፥ ጉድ ይወልዱ ።

ሁለት ጥፉ ፥ ካገር ይጥፉ ።

ሁሉ ሄዶ ፥ ተበተነ እህና እኔ ቀረነ አለ እያዘነ ።

ሁሉ በጇ ፥ ሁሉ በደጇ ።

ሁሉ ቢናገር ፥ ማን ይሰማል ።

ሁሉ አማረኝን ፥ ገበያ አታውጣት ።

ሁሉ አረሰ ፥ ማን ይሸምት ።

ሁሉ ያልፋል ፥ እስኪያልፍ ያለፋል ።

ሁሉ ያልፋል ፥ እውነት ብቻ ይተርፋል ።

ሁሉም ሰው መምሰሉ ፥ ባይታይ አመሉ ።

ሁሉም አካል ነው ፥ ግን እንደ አይን አይሆንም ።

ሁሉን ቢናገሩት ፥ ሆድ ባዶ ይቀራል ።

ሁልጊዜ ከመደንገጥ ፥ አንድ ጊዜ መሸጥ ።

ሂዳ ጉበት የነቧት ፥ ታናሽ ታላቅ ስደዱልኝ አለች ።

ሂድ አትበለው ፥ እንዲሄድ አድርገው ።

ሂድ ካገር ፥ ኑር ካገር ።

ሃይለኛ ዱቄት ከነፋስ ይጣላል ።

ሃይማኖት ከግብር ፥ ፀሎት ከፍቅር ።

ሃጢአት በንስሃ ፥ በደል በካሳ ።

ሀመሙ ቀርቶ ሞቱን በተወኝ ።

ሀመሙን የሸሸገ መድሃኒት የለውም ።

ህያዋን ለነገስታት ፣ ሙታን ለካህናት ይገብራሉ ።

ሆደ ሰፊ ፣ ነገር አሳላፊ ።

ሆደ ሰፊ ፣ ይሻላል ካኩራፊ ።

ሆዱ ናረት ፣ ሙያው ከጅረት ።

ሆዱ ፈሪ እግሩ ዳተኛ ፣ አዳም ሲዋጋ እርሱ ይተኛ ።

ሆዱን ያለ ፣ ሆዱን ተወጋ ።

ሆዳም ቢሸከም ፣ የበላ ይመስለዋል ።

ሆዳም ቢፈተፍት ፣ የጠገበ ይመስለዋል ።

ሆዳም ፣ ፍቅር አያውቅም ።

ሆዴ በጀርባዬ ቢሆን ፣ ገፍቶ ገደል በጣለኝ ።

ሆዴ ፣ ኑር በዘዴ ።

ሆዴ ፣ አታጣላኝ ከዘመዴ ።

ሆድ ሆዱን የምትል ወፍ አለች ፣ ምናለች ?

ሆድ ሆዴን የሚለውን ጌታ ያየዋል ፤ አይኔ አይኔ የሚለውን ሰው ያየዋል ።

ሆድ ፣ ለማታ በልቶ ለጧት ።

ሆድ ለባሰው ፣ ማጭድ አታውሰው ።

ሆድ ሲሞላ ፣ ራስ ባዶ ይቀራል ።

ሆድ ሲያር ፣ ጥርስ ይስቃል ።

ሆድ ሲያውቅ ፣ ዶሮ ማታ ።

ሆድ ባዶ ይጠላል ።

ሆድ እንዳሳዩት ነው ።

ሆድ ከሁዳድ ይሰፋል ።

ሆድ ወዶ ፥ አፍ ክዶ ፥ ክፉ ለምዶ ።

ሆድ የኔ ነው ሲሉት ፥ ቁርጠት ሆኖ ይገድላል ።

ሆድ ያበላውን ያመሰግናል ።

ሆድ ያባውን ፥ ብቅል ያወጣዋል ።

ሆድ ዘመድ ሳይወድ ፥ አፍ እህል ሳይለምድ ።

ሆድህና ልጅህ አይጥሉህ ።

ሆድህን ጎመን ሙላው ፥ ጀርባህን ለጠላት አታሳይ ።

ሆድና ግንባር አይሸሸጉም ።

ሆድን በጎመን ቢደልሉት ፥ ይለግማል ጉልበት ።

## - ለ -

ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ ።

ለሃብት መትጋት ሰውነትን ያከሳል ፤ ገንዘብን ማሰብ እንቅልፍ ይነሳል ።

ለሃጥእን የወረደ ፥ ለፃድቃን ይተርፋል ።

ለሂያጅ ፥ የለውም ወዳጅ ።

ለሆዳም በሬ ገለባ ያዝለታል ።

ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል ።

ለሆዴ ጠግቤ ፥ በልብሴ አንግቤ ።

ለሆድ ቁርጠት ብላበት ፤ ለራስ ምታት ጩህበት ።

ለላሙ መንጃ ፥ ለሽማው መቅደጃ ።

ለላሙ መንጃ ፥ ለሽማው መከንጃ ።

ለላም ቀንዷ አይከብዳትም ።

ለላም ከጥጃዋና ካቢላሟ ማን ይቀርባታል ።

ለላም ፡ የሳር ለምለም ።

ለላም ጥጃዋ ፡ ለአህያ ውርንጭላዋ ።

ለሌለው ፡ ምን ትለው ።

ለልጅ ሲሉ ይበሉ ፡ ለወገን ሲሉ ይጠሉ ።

ለልጅ አይስቁለትም ፡ ለውሻ አይሮጡለትም ።

ለልጅ ጥርስህን ፡ ለዝንብ ቁስልህን አታሳይ ።

ለልጅ ጨዋታ ፡ ለባለጌ ቧልታ ።

ለመሄድና ለመላወስ ፡ አዛዡ ራስ ።

ለመሆን ሳይሆን ፡ እንዴት ይሆናል ቢሆን ።

ለመሪህ አሳ ምሰል ።

ለመስራት የሚያፍር ፡ መብላት አይደፍርም ።

ለመስጠት አለመቸኮል ፡ ከሰጡም ወዲያ አለመፀፀት ።

ለመታማት ፡ መፍራት ።

ለመከራ ያለው መነኩሴ ፡ ዳዊቱን ሸጦ አህያ ይገዛል ።

ለሙት ፡ የለው መብት ።

ለሚመለከት ለሚያየው ፡ ሞት ቅርብ ነው ።

ለሚስት ያጎርሷል ፡ ለተመታ ይከፏል ።

ለማን አለው ፡ ፈጣሪ አለው ፤ ጠጅ ለሌለው ፡ ውሃ አለው ።

ለማን ይፈርዱ ? ለወደዱ ፤ አይደለም ለወደዱ ፡ ለወለዱ ።

ለማየት የፈለገ ፡ አይኑን ይገልጣል ።

ለማያውቅ ፎገራ ዱሩ ነው ።

ለማያውቅሽ ታጠኝ ።

ለማይሞት መድሃኒት አለው ።

ለማይሰዋ ሰው ፣ ስጡኝ ማለትን ማን አስተማረው ?

ለምሽት መብራት ፣ ለመከራ ጊዜ ብልሃት ።

ለምን ተከገፎ ፣ እምላክን ይገፎ ።

ለምን ያለው ስልቻውን ፣ ጫን ያለው ኮርቻውን ።

ለምን ጊዜው ነቀዝሽ ።

ለምኖ ለማኝ ፣ ቆቤን ቀማኝ ።

ለሞኝ ሰኔ በጋው ፣ መስከረም ክረምቱ ።

ለሞኝ ንገረው ፤ ምን ይሰማ ብዬ ? ለብልህ ንገረው ፤ ምን ይሳተው ብዬ ?

ለሞኝ ከሳቁለት ፣ ለቅዘን ከሮጡለት ።

ለሞኝ ከሳቁለት ፣ ለውሻ ከሮጡለት ።

ለሞኝ ጉድጓድ አያሳዩትም ፣ ቤት ነው ብሎ ይገባበታል ።

ለሞፈር ቆራጭ ፣ እርፍ አይታየውም በግላጭ ።

ለራሱ አያውቅ ነዳይ ፣ ቅቤ ለመነ ላዋይ ።

ለራሱ ጥላ ፣ ለእግሩ ከለላ ።

ለራስ ምታት ጨህበት ፣ ለሆድ ቁርጠት ብላበት ።

ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ።

ለራበው ሰው ቆሎ ፣ ለቁልቁለት በቅሎ ።

ለራት የማይተርፍ ዳረጎት ።

ለርስት ሴቶች ስንኳ ይሞቱበታል ።

ለስለባ የመጣ ፣ ልብስ ቢጥሉለት አይመለስም ።

ለሰበበኛ ቂጥ ፣ መረቅ አታብዛበት ።

ለሰባቂ ጆሮህን አትስጠው ።

ለሰው ልጅ ሲያበሉ ፣ ለውሻ ልጅ ያብሉ ።

ለሰው ሞት አነሰው ።

ለሰው ቢናገሩ መልሶ ለሰው ፣ ጫር ጫር አድርጌ አፈር ላልብሰው ።

ለሰው ብሎ መሞት ፣ እምላክነት ያሻል ።

ለሰው ብሎ ሲያማ ፣ ለኔ ብለህ ስማ ።

ለሰው ከበሬታው ሰው ፣ ለወጥ ማጣፈጫው ጨው ።

ለሳት ውሃ ፤ ለፀጉር ቡሃ ።

ለሴት ልጅ እስከ አርባ ቀን ሞቷን ፣ ከዚያ ወዲያ ሁብቷን ።

ለሴት ምክር አይገባትም ።

ለሴት ጠላ ፣ ለፈረስ ቆላ ።

ለስሱ ፍትፍት አሳይቶ እበት ያጎርሷል ።

ለስሟ መጠሪየ ቁና ሰፋች ።

ለሸማኔ ማገጃ ፣ ስለት ማረጃ ።

ለሹመት ካልመከሩለት ፣ ለጥርስ ካልከደኑለት ።

ለሺ ፍልጥ ፣ ማሰሪያው ልጥ ።

ለቀላል ምስጢር መንገር ፣ በቀዳዳ ጤፍ መቋጠር ።

ለቀባሪው አረዱት ።

ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው ፤ ቀንዱ ያከልክለው ።

ለቁንጫ ለምዕ ያወጣል ።

ለቂጡ ጨርቅ የለው ፣ ቆንጆ ያባብላል ።

ለቅልብልብ አማት ፥ ሲሶ በትር አላት ።

ለቅሶ ሳለ ከቤት ፥ ለቅሶ ይሄዳል ከጎረቤት ።

ለቅዘን እግር አንስተውለት ።

ለበራ ወለባ ፥ ለውሻ ገለባ ።

ለበጋ ጥጃ ውስ አነሰው ወይ ?

ለበግ ደጋ ፥ ለምቾት አልጋ ።

ለባብ እግር የለው ፥ ለሞኝ መላ የለው ።

ለቤት ሳማ ፥ ለውጭ ቂጤማ ።

ለቤት ሳንቃ ፥ ለሰው አለቃ ።

ለቤት ባላ ፥ ለችግር ነጠላ ።

ለብልህ አይነግሩ ፥ ለድመት አያበሩ ።

ለብልህ አይነግሩ ፥ ላንበሳ አይመትሩ ።

ለብዙ ፀሎት ፥ ማሰሪያው አቡነ ዘበሰማያት ።

ለተማሪ ቆሎ ፥ ለወታደር በቅሎ ።

ለተሚጋች መዘዘኛ ፥ የዳኛ ትእግስተኛ ።

ለተረታው ያበደረ ፥ እሳት ጨመረ ።

ለተራበ በግብር ፥ ለተበደለ በነገር ።

ለተሸሸገ ምግብ ፥ የተሸሸገ ሆድ አይጠፋለትም ።

ለተሾመ ይሚገቱለታል ፥ ለተሻረ ይመሰክሩበታል ።

ለተቀማጭ ፥ ሰማይ ቅርቡ ነው ።

ለተባባሰው ፥ ማጭድ አታውሰው ።

ለትሁዋን ልጓም ማጉረስ ፥ ላፈኛ ሰው መመለስ ።

ለቸኮለ ሰው ፤ ቀንጫ አስጨብጠው ።

ለነገረኛ ሰው ፤ ጀርባህን ስጠው ።

ለነገረኛ ነገር ተውለት ፤ ለሆዳም እህል አቅርብለት ።

ለኔ ፤ ነግ በኔ ።

ለንጉስ ያልረዳ ፤ ከባህር ያልቀዳ ።

ለአበባ ፤ የለው ገለባ ።

ለአምላክ ልንገረው ፤ ለማያስቀረው ።

ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል ።

ለእሳት እንጨት ካልነሱት አይጠፋም ።

ለእሳት ፍላት ፤ ለጮማ ስባት ።

ለእባብ እግር የለው ፤ ለባዳ ውል የለው ።

ለእብለት ስር የለው ፤ ለእባብ እግር የለው ።

ለእበጥ ፍላት ፤ ለእንጨት እሳት ።

ለእውር ዝማሜ ፤ ለመላጣ ጋሜ ።

ለእጅ ርቆ ፤ ለአይን ጠልቆ ።

ለእግሩ የተጠየፈ ፤ ለቂጡ አተረፈ ።

ለእግር የፈሩት ፤ ለቂጥ ይተርፋል ።

ለእግዚአብሐር የቀንቀን ለዕድቅ ፤ ለጌታ የቀንቀን ለወርቅ ።

ለከለላ ጥላ ፤ ቢርብህ ብላ ።

ለካህን ጥምቀት ፤ ለገበሬ ግንቦት ።

ለከፋት ያደለው ፤ አሳዳጊ የበደለው ።

ለኩ መሳቢያ ፤ ወፍጮ ማላሚያ ።

ለወሬ ወዳጁ ወሬ ፣ ለመነኩሴ ጥሬ ።

ለወሬ ፣ የለው ፍሬ ።

ለወሬ የለው ፍሬ ፣ ለአበባ የለው ገለባ ።

ለወሬ የቸኮለ እናቱን በመንገድ ላይ ይረዳል ።

ለወታደር ፣ ሰፊ መንደር ።

ለወይዘሮ ፣ መልካም ዶሮ ።

ለወዲላ ፣ መልካም ዱላ ።

ለወዳጅ የማር ወለላ ፣ ለጠላት አሜኬላ ።

ለወዳጅና ለአይን ፣ ትንሽ ይበቃዋል ።

ለወጡም እዘኑለት ፣ አንዳንድ ጊዜ ዶረቅ ጉረሱለት ።

ለወጡም እዘኑለት ፣ ከዶረቁም ብሉለት ።

ለዋንጫ ቡሽ ፣ ለውሃ ጉሽ የለውም ።

ለውሻ ፣ ምሳ የለው ራት ብቻ ።

ለውሻ ሞት ፣ ፊት አይነጩለትም ።

ለውሻዬ ያልሁትን ፣ ልጄ ቢበላብኝ አልወድም ።

ለውጡኝ ባይ ፣ የሚሻለውን አውቆ ።

ለዘመዱ ፣ ያዝናል ሆዱ ።

ለዝናም ጌታ ውሃ ነሱ ።

ለይቶ እንደፈፋ ፣ አንጓሎ እንዳረፋ ።

ለይቶት አባ ንጉሢ ።

ለደሀና ሰው ፣ ዋጋ አነሰው ።

ለደብተራ ፣ መቋሚያና ጭራ ።

ለደግ ንጉስ ፣ እለት እለት ማልቀስ ።

ለዳርቻው ሲሳሱ ፣ መካከሉን ተነሱ ።

ለዳባ ለባሽ ፣ ነገርህን አታበላሽ ።

ለዳኛ የነገሩት ፣ በርጥብ ያቃጠሉት ።

ለድሃ ፣ ማን ሰጠው ውሃ ።

ለድህነት የፈጠረው ፣ ቢነግድ አያተርፍም ።

ለድሪ ያሉት አንገት ፣ ለአሽከት ።

ለድካም የጣፈኝ ፣ ብነግድ አይተርፈኝ ።

ለዶሮ ሲነግሩ ፣ ምጥማጥ ይሰማል ።

ለጆሮ ጥርስ ፣ ለሆዳም ስስ ።

ለገላጋይ ደም የለውም ።

ለገበሬ ፣ መልካም በሬ ።

ለገቢህ ተንገብገብ ።

ለገዳም የረዳ ፣ አይጎዳ ።

ለጉንዳን ደም የለው ፣ ለዝንብ ቤት የለው ።

ለጉንዳን ደም የለው ፣ ለገንዘብ ቤት የለው ።

ለጋስ ቢለግስ አበደረ እንጂ እንዲያው አልሰጠም ።

ለጠላትህ እንደ ዳቦ እስኪገምጥህ አትመቸው ።

ለጠጪ ሰው ፣ የመጠጥ ወሬ አውራው ።

ለጥቅምት ያልሆነ ቀሚስ ፣ ይበጣጠስ ።

ለጨቅጫቃ ሰው ከማበደር ፣ ይሻላል በጂ ይደር ።

ለያም ግድፈት ፣ ለባል ሽረት ።

ለፈረስህ አንገት ፣ ለጋሻህ እምብርት ።

ለፈሪ ሜዳ አይነሱም ።

ለፍቅር ብትተኛ ፣ ለጠብ አረገዘች ።

ለፍየል ቆላ ፣ ለሙክት ባቄላ ።

ሊሸገር ቢያምረው ይዋኛል ፣ ሊሟገት ቢያምረው ይዳኛል ።

ሊበሉ የፈለጉትን አሞራ ፣ ስሙን ይሉታል ጅግራ ።

ሊወጋ የመጣ ፣ ጌታዬ ቢሉት አይመለስም ።

ሊያልፍ ውሃ ፣ አደረገኝ ድሃ ።

ሊያስቡት አይገድም ።

ሊጣላ የመጣ ፣ ሰበብ አያጣም ።

ላህያ ማር አይጥማት ።

ላለው ቅንጭብ ያረግዳል ።

ላለፈ አይፀፀቱም ፣ ለሚመጣው አይበለጡም ።

ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራለትም ።

ላሊበላ ሄዶሽ ከህንፃው ብትሰፍሪ ፣ አይገኝም ዕድቅ አለ ባህሪ ።

ላሊበላ ፣ አደራውን አይበላ ።

ላሊበላ ፣ የቃሉን አይበላ ።

ላሊበላን ካላጠገቡት ይጮሃል ፣ ሎሌም ካልሰጡት ይከዳል ።

ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው ።

ላመት ልብስ ፣ ለእለት ጉርስ ።

ላም ሲበዘበዝ ፣ ጭራዋን ያዝ ።

ላም በረቱን ፣ የሰው ልጅ አባቱን አይረሳም ።

ላም ባልዋለበት ፣ ኩበት ለቀማ ።

ላም ነጂዋን እንጂ ጌታዋን አታውቅም ።

ላም አለች በደረጣ ፣ ወተቷ ምን ይነጣ ።

ላም አለኝ በሰማይ ፣ ወተቷንም አላይ ።

ላም እሳት ወለደች ፣ እንዳትልሰው ፈጃት ፣ እንዳትተወው ልጅዋ ሆነባት ።

ላም ከወንዝ ፣ ልጅ ከቦዝ ።

ላም የዋለችበትን ትመስላለች ።

ላሳር የጣፈው ፣ ቢነግድ አይተርፈው ።

ላታመልጠኝ ፣ አታሩጠኝ ።

ላታገኝ አትመኝ ፣ ላታጣ አትቆጣ ።

ላትከፍል አትዋስ ፣ ላትደርስ አትገስግስ ።

ላንበሳ አይመትሩ ፣ ላዋቂ አይነግሩ ።

ላንድ ብርቱ ፣ ሁለት መድሃኒቱ ።

ላንድ አራሚ ፣ ዘጠኝ ቋሚ ።

ላንድ ጭቃ አገር ዘጠኝ ምስለኔ ።

ላያቱ እዳ ፣ ላማቱ ፍሪዳ ።

ላያጠግቡ መጋበዝ ፣ ላይገድሉ ካራ መምዘዝ ።

ላያጥብ አይለብስ ፣ ላያርም አያርስ ።

ላይሆን ቤት ፣ በበአል ስፌት ።

ላይሆን ዘመድ ፣ ገንዘቤንም አልሰድ ።

ላይሉኝ ቸር ፣ በየቦታው ስፈነቸር ።

ላይሉኝ ወሶ ፣ ደርሼ ነበር ከረጋ ለቅሶ አለ ጠይብ ።

ላይምረው ፣ አማሰነው ።

ላይሞት ይፈራል ፣ ላይድን ይሸሻል ።

ላይቀር ሞቱ ፣ መንጠራራቱ ።

ላይቀር ሳቁ ፣ ችኩ ።

ላይቀር ጣጇው ፣ አታራፍጅው ።

ላይበላው ፣ አበላሸው ።

ላይቶች አይፈርድ ፣ ላያተርፍ አይነግድ ።

ላይችል አይሰጥም ፣ ላይጠግን አይሰብርም ።

ላይን የሚከፋ ፣ ላፍንጫ የሚከረፋ ።

ላይንና ለወዳጅ ፣ ጥቂት ይበቃል ።

ላይኛው ከንፈር ለከርከር ፣ ታችኛው ከንፈር ለምስክር ።

ላይዘሩ አያርሱ ፣ ካላረሱ አያጎርሱ ።

ላይፈሩ ቁጣ ፣ ከእብደት አንድ ነው ።

ላገልጋይ ትእግስት ፣ ለባለቤት መጠቃት ።

ላገሩ እንግዳ ፣ ለሰው ባዳ ።

ላገሬ ሰው እንኳን ነጋሪት አታሞ አይሰጠው ።

ላጠፋ ምህረት ፣ ላጣ ቸርነት ።

ላፈኛ ሰው መመለስ ፣ ለትሁዋን ልጓም ማጉረስ ።

ላፍላ ፣ የለው ጎፍላ ።

ሌሊት ፣ የምክር እናት ።

ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል ።

ሌባ ቢያዩኝ እስቅ ፣ ባያዩኝ እሰርቅ ይላል ።

ሌባ ተይዞ ዱላ ጥየቃ ።

ሌባ እናት ፣ ልጅዋን አታምነውም ።

ሌባ ውሻ ባፏ ሊጥ ፣ በወገቧ ፍልጥ ።

ሌባና ሌባ ፣ ተጣሉ በሰው ገለባ ።

ሌባን ሌባ ቢሰርቀው ፣ ምን ይደንቀው ።

ሌት ከጅብ ፣ ቀን ከሀዝብ ።

ልማ በስሉስ ፣ ጥፋ በስሉስ ።

ሊማድ ሲቀር ፣ ምስህ ቅበር ።

ልበ ሰፊ ፣ ነገር አላፊ ።

ልበ ሳንባ ዶሮዬ ።

ልባልባ ታጥቆ አዛባ ፣ ሱሪ አውልቆ ፈረስ ጋለባ ፣ ራስ ላጭቶ ወለባ ።

ልብ ሲያውቅ ፣ ገንፎ ያንቅ ።

ልብ ሲያውቅ ፣ ጥርስ ከደመኛው ጋር ይስቃል ።

ልብ ሳይገዙ ፣ ነገር አያበዙ ።

ልብ እንቅርትን ለማየት ይመኛል ።

ልብ ከጎንጅ ፣ ትምህርት ከደጅ ።

ልብ ካዘነ ፣ እንባ አይቸግርም ።

ልብ ፣ ካጥባቂ ፈረስ ይስባል ።

ልብ የሌላት ውሻ ፣ ማር ትቀላውጣለች ።

ልብ የሚገኝ በስልሳ ፣ ገንዘብ የሚገኝ በሰላሳ ።

ልብ ያለው ፣ አገሩ ሰማይ ነው ።

ልብ ያሰበውን አፍ ይናገረዋል ፣ አይን ያየውን እጅ ይሰራዋል ።

ልብስ ይፈጃል ሌት መልበስ ፤ ወጥ ይፈጃል መኀራረስ ።

ልብስህን በውሃ ፥ ገንዘብህን በድሃ ።

ልብና ነፋስ ፥ ከሁሉ ያደርሳል ።

ልትደርቅ የደረሰች ምንጭ ፥ ጭልጭል ትላለች ።

ልዩ ስጋ ፥ በመንጋጋ ።

ልጁን በራብ ፥ የእንጀራ ልጁን በጥጋብ ።

ልጅ ለሳቀለት ፥ ውሻ ለሮጠለት ።

ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች ።

ልጅ ለወለደው ፥ ሙቅ ላሞቀው ።

ልጅ ሲያረጅ ፥ አባት ይጦራል ።

ልጅ ቢያስብ ምሳውን ፥ አዝማሪ ቢያስብ ጠላውን ።

ልጅ ቃርጣጣ ፥ እህል ከዘባጣ ።

ልጅ ቃጉል ፥ እህል ከጉራንጉር ።

ልጅ አባቱን ገደለ ቢለው ፥ የኔ ልጅ እንዳይሰማ አለው ።

ልጅ አይወለድ ፥ እውነት አይፈረድ ።

ልጅ እንዳባቱ ፥ ሰው እንደቤቱ ።

ልጅ ከዋለበት ፥ ሽማግሌ አይውልም ።

ልጅ ካባቱ ፥ ሾተል ካፎቱ ።

ልጅ ያለ ፥ ልጅ አከለ ።

ልጅ ያለ እናት ፥ ቤት ያለ ጉልላት ።

ልጅ ያባቱን ፥ ወቄራ ያፎቱን ።

ልጅ ያቦካው ፥ ለራት አይበቃም ።

ልጅ ይወለዳል ከቦዝ ፣ ላም ይገዛል ከወንዝ ።

ልጅ ደረሰ ፣ ቤት ፈረሰ ።

ልጅህንና አትክልትህን ፣ ተጠባበቅ ጎረቤትክን ።

ልጅና ቂስ ፣ በሰው ገንዘብ ያለቅስ ።

ልጅና ጥሬ ፣ አይተጣጡም ።

ልጅና ጠጣ ፣ ውሃ ይጠጣ ።

ልጅን መርገምና ራስጌ መሽናት ፣ ተመልሶ ጉዳት ።

ልጅን በጡት ፣ እህልን በጥቅምት ።

ልግመኛን መምከር ፣ ውሃ በወንፊት ማኖር ።

ልግም እግዜር አይወድም ።

ልጓም ለቆ ቹቹ ።

ልጡ የተራሰ ፣ መቃብሩ የተማሰ ።

ልፉ ያለው ፣ አንድ እንጨት ያስራል ።

ሎሌ ሲከብር ጌታውን ይከሳል ፤ ሙክት ሲሰባ ሾተል ይልሳል ።

ሎሌና አሞሌ ፣ ካዘዙት ይውላል ።

ሎሚ ካልመጠጡት ፣ እንቧይ ነው ።

ሎሚና ትርንጎ ሞልቶ ባገር ፣ እንቧይ ታሸታለህ የድሃ ነገር ።

- መ -

መሄድ መሄድን እያደራጀሁ ፣ እንደ ጉሬዛ ከሬት አረጀሁ ።

መሄድ መመላለስ ፣ ካሰቡት መድረስ ።

መሄድ መነሳት ፣ መከተል መሸኘት ።

መሄድ በጋ ነው ፣ መቀመጥ ክረምት ነው ።

መሄድ የለ ዛቻ ብቻ ፣ መስራት የለ አሳብ ብቻ ።

መሄድ ያማረው እራቱን በጨረቃ ይበላል ።

መለመን የለመደ መላስ ፣ በህልሙ አቁማዳ ይዋስ ።

መላ እንደ ሴት ፣ ግርማ እንደ ሌሊት ።

መላከተኛ ካጤ ቤት ይገባል ።

መልከኛው ኮሶ ቢጠጣ ፣ ጨሰኛው አስቀመጠው ።

መልኩ የኔ ፣ ግብሩ ያረመኔ ።

መልካም ልብ አይነካም ።

መልካም ሰሪ በልጆቹ ፣ የጨረቃ ንጋት በወፎቹ ይታወቃል ።

መልካም ሱሪ ፣ ለተማሪ ።

መልካም ቆንጆ ፣ የላት መቀናጆ ።

መልካም በሬ ለእርሻ ፣ ደማም አያሻ ።

መልካም ተመኝ ፣ መልካም እንድታገኝ ።

መልካም ወገን ፣ የፀሃይ ውጋገን ።

መልካም ወጥ ፣ እጅ ያስመጥጥ ።

መልካም ጭራ ፣ ለደብተራ ።

መልክ በግምት ይገኛል ፣ ልብ ትልቅ ይመኛል ።

መልኳ ባያምር ፣ አመሏ ይመር ።

መመራመር ፤ ያገባል ከባህር ።

መመሳሰል የጋራ ነው ።

መምሬ ፣ አይበሉም ጥሬ ።

መሪ የሌለው ጠንባሳ ፣ ምርኩዝ የሌለው አንካሳ ።

መራጭ ፣ ይወድቃል ከምራጭ ።

መሬት ሲያረጅ ፣ መጭ ያበቅላል ።

መሬት በድንበር ፣ ውበት በከንፈር ።

መሬት ባቅጣጫ ፣ መልክ ባፍንጫ ።

መሬት እናት ፣ ዘር አባት ።

መርጦ ይገዟል ፣ ዋጋ ያበዟል ።

መርፌ መግቢያዋን እንጂ ፣ መውጫዋን አታይም ።

መርፌ ቢሰበሰብ ማረሻ አይሆንም ።

መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ ለብዙ ሰው ትጠቅማለች ።

መሰረት ነዋሪ ፣ መሪና አስተማሪ ።

መሰስ ሲል ፣ ምን ደስ ይል ።

መሳሳሚያ ከንፈር ፣ መገናኛ ድንበር ።

መስራት እንጂ ፣ ማፍረስ አያቅትም ።

መስተዋት ፊት ያሳያል ፣ መሰንበት ሁሉን ያሳያል ።

መስተዋት ፊት ያሳያል ፣ መሰንበት ይበጃል ።

መስከረም ባበባው ፣ ሰርግ በጭብጨባው ።

መስጠት አያውቅ እራት ፣ መምታት አያውቅ አናት ።

መስጠት የማያውቅ የቁና እኩል ።

መሶብ ሰፍቼ ፣ ለአጤ አበርክቼ ።

መሸሽማ አንበሳም ይሸሻል ፣ መለስ ያለ እንደሆን ሰውን ያበላሻል ።

መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል ።

መቀመጥ ፡ መቆመጥ ።

መቀመጥ በና ነው ፤ መሄድ በልግ ነው ።

መቃ እንዲያ ሲያምር አያፈራ ፡ ወርቅ ቢሞላ አይዘራ ።

መቃን ከመግጨት ፡ ዝቅ ብሎ መግባት ።

መቃዠትና መስከር ፡ ላይመልሱ መበደር ።

መበለት በቁስ ፡ ገበሬ በንጉስ ።

መብሉ እኩል ፡ ስራው ስንኩል ።

መብላት ከሁለት ፡ መፍረድ በውነት ።

መብላት ከባእድ ፡ ምክርን ከዘመድ ።

መብሌ ስንቆ ፡ ምርኩዜ ሽንበቆ ።

መብልን ይገኛ ቅልውጤን ረሳሁት ።

መብል ያለመጠጥ ፡ እንጀራ ያለወጥ ።

መብልን ከሰው ቤት ፡ መኝታን ከቤት ።

መብልን ከባእድ ፡ ሃዘንን ከዘመድ ።

መብረቅ የመታውን ወዘት አስተኛው ።

መብራት ለጨለማ ፡ አፍንጫ መያዝ እንዳይገማ ።

መተው ፡ ነገሬን ከተተው ።

መታለል ፡ ገደል መንከባለል ።

መታፈር ፡ በከንፈር ።

መቼ ገባህ ፊት ፡ ምን በላህ ፍትፍት ።

መች መጣሽ ሙሽራ ፡ መች ቆረጠምሽ ሽንብራ ።

መነኩሴ በቆብ ፡ ወንበር በከታብ ።

መነኩሴ ካልሞተ ፣ ስንዴ ካልሸተ አይታወቅም ።

መነዛነዝ ፣ ያመጣል መዘዝ ።

መነገድ ለማትረፍ ፣ መማር ለመፃፍ ።

መናኝ ለነፍሱ ፣ አዳኝ ለጥርሱ ።

መናጂ የሌለው በሬ ፣ ለምድ የሌለው ገበሬ ።

መናገር መልካም ነው ፤ ማዳመጥ ይበልጣል ።

መንደር በልጆች ፣ አገር በገበሬዎች ።

መንደር ከዋለ ንብ ፣ አደባባይ የዋለ ዝንብ ።

መንገደኛ ከስንቁ ፣ ነጋዴ ከወርቁ ።

መንገድ ለቀደመ ፣ ውሃ ለገደበ ።

መንገድ ሳለ በዱር ፣ በቅሎ ሳለ በእግር ።

መንገድ ባሳብ አይደረስም ።

መንገድ ከሸንት ይቀራል ።

መንገድ ካገር ልጅ ፣ ምክር ከጨዋ ልጅ ።

መንገድ ካገር ልጅ ፣ ስደት ከሹም ልጅ ።

መኖር ማለት ፣ ብርሃንና መሰንበት ።

መኖር ማለት ፣ ብርሃንና መስተዋት ።

መኖር በከንቱ ፣ ሰው አለቤቱ ።

መኖር በከንቱ ፣ ያለ ባለቤቱ ።

መከራና እዳ ፣ እንግዳና ሞት ፣ በድንገት ።

መከራና ጉም እያደር ይቀላል ።

መከራው ያላለቀለት በሬ ፣ ከሞተ በሁዋላ ቆዳው ነጋሪት ይጠፈራል ።

መከፈንና መሸፈን ፣ እግዜርን ማመን ።

መካር የሌለው ንጉስ ፣ አላንድ አመት አይነግስ ።

መከዳትና መኮብለል ፣ ወድቆ መንከባለል ።

መከፈልት ሲሹ መቅሰፍት ።

መወለድ ካለ ማዘን አይገድም ።

መውጫህን ሳታይ አትግባ ።

መዝገብ ቢጠፋ ባገር ፣ ቤት ቢላላ በማገር ።

መዝጊያ የሌለው ቤት ፣ ሌሰኛ ሴት ።

መጠዋ ለጨዋታ ፣ ወንድም ለግርግርታ ።

መጠዋ ከጨዋ ልጅ ፣ ምክር ከድሃ ልጅ ።

መጠዋ ከጨዋ ልጅ ፣ ምክር ካገር ልጅ ።

መጣፍና ተማሪ ፣ ቀለበትና ድሪ ።

መጥረቢያው የተውሶ ፣ ጠፋ ተመልሶ ።

መጥፊያው ፣ መልሚያው መስሎ ይታየዋል ለሰው ።

መጥፎ ወሬ ይበራል ፣ መልካሙ ይተኛል ።

መጨነቅ የመጠበብ እናት ።

መጫር ያበዛች ዶሮ የመታረጃዋን ቢላዋ ታወጣለች ።

መጭ ፣ መጭ ከሚሉት በቅሎ መጫሚያ ።

መፍራት ለመታማት ።

መፍታት ሳለ መሞት ።

ሙሽራ በሚዜ ፣ ንስሃ በትካዜ ።

ሙሽራዋስ እኔ ፣ ዶሮዋን ማን በላት ካለኔ ።

ሙቅ ውሃና የሰው ገንዘብ አይጠቅምም ።

ሙታንን ከማመስገን ፣ ህያዋንን ማስተንተን ።

ሙት መውቀስ ፣ ድንጋይ መንከስ ።

ሙት ይዞ ይሞታል ።

ሙዝ ላጥ ፣ ዋጥ ።

ሙግት ላፍለኛ ፣ አብቹ ለጌኛ ።

ሙግት ያውቋል ፣ ይልቋል ።

ሚስቱ ከፉ ባቄላ እራቱ ፣ ብሳና እንጨቱ ፣ ሃዘን ነው እቤቱ ።

ሚስቱ ደግ ስንዴ እራቱ ፣ ወይራ እንጨቱ ፣ ደስታ ነው እቤቱ ።

ሚስቱን ጠልቶ ካማቱ ፣ ልጁን ከሶ ካባቱ ።

ሚስት ባታብል ባሏን ትወዳለች ።

ሚስት ከፈቷት ባዳ ፣ ማሽላ ከተቆረጠ አገዳ ።

ሚስትህ አረገዘች ወይ ቢለው? ማንን ወንድ ብላ ።

ሚስትህን ስደድ ፣ በሬህን እረድ ፣ ይላል የባለጌ ዘመድ ።

ሚስትና ዳዊት ፣ በብብት ።

ሚዜ ቢከተል አሽከር ይመስላል ።

ሚዳቋ ቀስ ብላ ስትሄድ የተያዘች ትመስላለች ።

ሚዳቋ እንደ አንበሳ እምህ ብላ ተሰንጥቃ ሞተች ።

ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር ።

ማልደው ቢነሱ ፣ እኩለ ቀን አይደርሱ ።

ማማት የለመደ አፍ ሲያለግ ያድራል ።

ማማው ሞረት ፣ ማሽላው ቅንብቢት ።

ማማው ከጉልበት ፣ ማሽላው ከእንብርት ።

ማምሻም እድሜ ነው ።

ማረግ ቢስ ፣ እራቱ ገሚስ ።

ማረፍና መራገፍ ፣ እየበሉ መንገፍገፍ ።

ማሩን አምሮ ፣ ውተቱን አጥቁሮ ።

ማር ሲሰፍሩ ፣ ማር ይናገሩ ።

ማር ሲበዛ ይመራል ።

ማር ሽጦ ምን ይበሏል ፣ ልጅ ጠልቶ ምን ይወዷል ።

ማር ሽጦ ምን ይገዟል ፣ ልጅ ጠልቶ ምን ይወዷል ።

ማር ነክቶታል ብለህ እጅህን አትላስ ።

ማር አገባ አገባ ፣ ገደል ገባ ።

ማርና ቅቤ ይጣፍጣሉ ፣ ከየት ይገኛሉ ።

ማርና ንብ ፣ ዕህፈትና ንባብ ።

ማርና ውተት ፣ ምን አገናኝቶት ።

ማሽላ ለማሽላ ፣ ተያይዞ ቆላ ።

ማሽላ ሲያር ይስቃል ።

ማሽላና ዘንጋዳ ፣ መከታና ጓዳ ።

ማቅ ይሞቃል ፣ ሻሽ ይደምቃል ፣ ገቢውን ባለቤት ያውቃል ።

ማባበል ፣ መቅለል ።

ማባበልና ማንቆሻበል ፣ ማሞኘትና መደለል ።

ማተብና እንገት ፣ ክታብና ደረት ።

ማን ሊስምሽ ፣ ታጥጠሙጪአለሽ ።

ማን ቢያሮጠኝ ፣ ሱፋጭ ቆረጠኝ ።

ማን አለ መርማሪ ፣ አለ ፈጣሪ ።

ማን ያውራ የነበረ ፣ ማን ያርዳ የቀበረ ።

ማን ያውቃል ባላገር ፣ ማን ያጠብቃል ማገር ።

ማን ያውቅ አገር ፣ ማን ይጠብቅ ማገር ።

ማን ይሙት ጠላት ፣ ማን ይኑር አባት ።

ማንን ታሸንፋለህ? ሚስቴን ።

ማወቅ መላቅ ፣ አለማወቅ መናቅ ።

ማወቅ እናውቃለን ፣ ብንናገር እናልቃለን ።

ማውራት ነው ሴትነት ፣ መስራት ነው ወንድነት ።

ማጀት በጎረሰ ፣ ደጃፍ በመለሰ ።

ማግኘት ማውጣትን ያስለምዳል ።

ማግኘት ማውጣትን ይመልሳል ።

ማጣት ከሰማይ ይርቃል ።

ማጣትና ማግኘት ጆሮ ለጆሮ ።

ማፈር ከሌለ ክብር የለም ።

ሜ ባልኩ ፣ ፍየል ከፈልኩ ።

ሜዳ መራመድ ሳታውቅ ፣ መሰላል መውጣት ማን አስተማራት ?

ምለህ በክርስቶስ ፣ ተገዝተህ በቄስ ።

ምላስ ቢጥም ፣ ቀዶ ይጠቅም ።

ምላስ ይቀባል ፣ ጥርስ ይወጋል ።

ምላጭ ለመላጫ ፣ ጠፍር ለመለመጫ ።

ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ ? ውሃ ቢያንቅ በምን ይውጡ ?

ምርቅና ፍትፍት ።

ምርት ከገለባ ፣ ግዳይ ከሰለባ ።

ምሳሌህ ሁሉ አንካሳ ነው ።

ምስለኔ ፣ ሁን እንደኔ ።

ምስር መዝራት ሞያ ማጣት ፣ አተር መዝሩት ወይ ብልሃት ፣ አለች ጠጣ ።

ምስር ፣ ብልት ይቀስር ።

ምስር እራቱ ፣ ምስር ቢያጣ ሞቱ ።

ምስክር ለበለጥ ፣ አውድማ ለመለጥ ።

ምስክር በበለጠ ፣ ባቄላ ባፈጠጠ ።

ምስክር ቢያድር ይለወጣል ፣ ሽንፍላ ቢያድር ይመለጣል ።

ምስክር ከተጠራ ፣ መስዋእት ከተሰራ ።

ምስክር ያለው ሙግት ፣ አያዳግትም ለመርታት ።

ምስጋና አዋቂን ያበረታል ፣ ቂልን ያሳብዳል ።

ምስጢር የባቄላ ወፍጮ አይደለም ።

ምስጥ ፣ ከምድር ውስጥ ።

ምቀኛ ጠላቱን ይተክል ፣ ራሱን ይነቅል ።

ምነው ቢገዙ ፣ መድን ካበዙ ።

ምናልባት ቢሰበር አናት ቅቤ ሻ ፣ ለመተኮሻ ።

ምን በእግሩ ቢመጣ ፣ በእጁ እንዳይመጣ ።

ምን ቢነግሱ ፣ በጅ አይካሱ ።

ምን ቢከፉ ፣ አሳብ ነው ትርፉ ።

ምን ቢወቅሱ ፣ በእጅ አይከሱ ።

ምን ቢዋደዱ ፣ እየቅል ነው መንገዱ ።

ምን ቢያርሱ ፣ እንደ ጎመን አይጎርሱ ።

ምን ቢያርሱ ፣ ድንበር አያፈልሱ ።

ምን ቢያስጠምዱ በዘጠና ፣ ከቤት አይወጣ ቀጠና ።

ምን ቢያውቁ ዳኛ አይሆኑ ፣ ምን ቢያምሩ ሙሽራ አይሆኑ ።

ምን ቢፈሩ ፣ ከሞት አይቀሩ ።

ምን ያመጣ ድሃ ፣ ምን ያገሳ ውሃ ።

ምን ያመጣል ሰኔ ፣ ምን ይሰራል ቦዘኔ ።

ምን ይሰማ ጆሮ ፣ ምን ይውጥ ጉሮሮ ።

ምን ይበሏል ? ነጭ ፤ ምን ይጠጧል ? ጠጅ ።

ምን ይዞ ጉዞ ።

ምንም በሙቱ ፣ አራድማ ሽምቱ ።

ምንም ቢሆን ስር ነው እንጂ እጢ አይደማም ።

ምንም ቢጠም መንገድ ፣ ምንም ቢከፋ ዘመድ ።

ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ ።

ምንም ብታውቅ ፣ ከዳኛ ጋራ አትሟገት ።

ምንም ብታፈገፍጊ ፣ ከግድግዳ አታልፊ ።

ምንም ብትሞቺ ፣ እንዴት አደርሽ አንቺ ።

ምንም ብጠላው በወንድሜ ግንባር ደም አልይበት ።

ምንሽም ምንሽም አያምረኝ ፣ ከመሄድሽ በቀር ።

ምንጃር ጤፍ ተወቃ ቢሉት ፣ ሽንኮራ ሆኖ እብቁ አይኔ ገባ አለ ።

ምኞትና ጉም ፣ አይጨበጥም ።

ምከረው ምከረው ፣ ባይሰማህ ንከረው ።

ምከረው ምከረው ፣ እንቢ ቢል መከራ ይምከረው ።

ምክር ዝክር በምድር ፣ ልጇ ተመከር ።

ምክር ከሽማግሌ ነው ፣ መሻገር ከጎበዝ ነው ።

ምክር ከድሃ ነበርሽ ፣ ማን ቢሰማሽ ።

ምድር ሲደለደል ፣ ማሳ ሲታደል ።

ምድር በዛፍ ፣ ህግ በመፅሃፍ ።

ምድር በዶሮ ፣ ያውስ ማን ገብሮ ።

ምድር በአለቃ ፣ ሰማይ በጨረቃ ።

ምጡን እርሺው ፣ ልጁን አንሺው ።

ምጥ ለናቷ አስተማረች ።

ምፅዋት ፣ የእለት እራት ።

ሞት ላይቀር ፍርሃት ፣ አመል ላይቀር ቅጣት ።

ሞት ርስት ነው ፣ መፈራቱ ለምንድነው ።

ሞት ሲደርስ ቂስ ፣ ጦር ሲደርስ ፈረስ ።

ሞት በአቤል ፣ ተዝካር በሮቤል ።

ሞት በእንቅልፍ ይለመዳል ።

ሞት በጥር ፣ በነሃሴ መቃብር ።

ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል ።

ሞት ባልቀረለት ፣ ምክንያት ባልሆነበት ።

ሞት አይለመድ ፣ ጎሽ አይጠመድ ።

ሞትን ማሰብ ፣ ከሁሉ መሰብሰብ ።

ሞትን የሰጠ ቀባሪ አይነሳም ።

ሞትን ያህል እዳ ፣ መቃብርን ያህል እንግዳ ።

ሞኝ ለራሱ ያውቃል ።

ሞኝ ለጠበቃው ምስጢር ይሸሽጋል ።

ሞኝ ሲናገር ብልህ ያዳምጣል ።

ሞኝ በብልህ ይስቃል ።

ሞኝ ቢቆጡት የመቱት ይመስለዋል ።

ሞኝ ቢፈርዱ ፣ ሞኝ ይወልዱ ።

ሞኝ ባያፍር ፣ የሞኝ ዘመድ ያፍር ።

ሞኝ ተላላ አበላል የት ያውቃል ፣ ፈትፍተው ሲያጎርሱት መዋጥ ያቅተዋል ።

ሞኝ ተናጋሪ ፣ ከፉውን በፊት ደጉን በሁዋላ ።

ሞኝ ነጋዴ በራሱ መቀማት ሳያዝን በጓደኛው ማምለጥ ይቆጨዋል ።

ሞኝ አሞራ ያባቱን ዋሻ ይጠየፋል ።

ሞኝ አሳላፊ ወንድሙን ይጎዳል ።

ሞኝ አንዳጅ ፣ ግንዱን በውስጥ ጭራሮውን በላይ ።

ሞኝ አያውቁብኝ ባይ ።

ሞኝ ከመካሩ ቤት እሳት አይሞቅም ።

ሞኝ ከመካሪው ፣ እውር ከመሪው (ይጣላል) ።

ሞኝ ከመካሪው ይጣላል ።

ሞኝ ከመውለድ ፣ ማስወረድ ።

ሞኝ ከጠገበበት አይወጣም ።

ሞኝ ካመረረ ፥ በግ ከበረረ ።

ሞኝ ካገደደ ፥ ልጅ ከለመደ ።

ሞኝ ወርውሮ ቢስት ፥ የወጋ አይመስለውም ።

ሞኝ ወታደር ፥ ሚስቱን ጥሎ መንደር ።

ሞኝ ውሃ ሲወስደው ይስቃል ።

ሞኝ የለቱን ፥ ብልህ ያመቱን ።

ሞኝ የመከሩት እለት ፥ ቁንጫ የጠረጉት እለት ይብሳል ።

ሞኝ የተከለውን ብልህ አይነቅለውም ።

ሞኝ ያገኘው ፈሊጥ ፥ ውሻ ያገኘው ሊጥ ።

ሞያ የለ መልክ ብቻ ፥ አመል የለ ነገር ብቻ ፥ አስቸጋሪ ለጋብቻ ።

ሞፈር ቆራጭ እርፍ አይታየውም ።

## - ረ -

ረባዳ ቤቱ ፥ ገራም ሚስቱ ።

ረኀሙን ባላማ ፥ አጭሩን በጫማ ።

ረኀም ባይፈራ ፥ አጭር ባይኮራ ።

ረኀም ጦር ባይወጉበት ፥ ያስፈራሩበት ።

ረኀም ጭራ ፥ ከኀረቤት ያጣላ ።

ረኀምና ቀፋፋ ፥ ገደልና ፈፋ ።

ሩቅ አሳቢ ፥ ቅርብ አዳሪ ።

ሩቅ አገር ለውሸት ይመቻል ።

ሩዋጭና በራሪ ፥ ንፉግና ፈሪ ።

ራሱን ለተላጨ ፣ ፊቱን ለነጨ ።

ራሱን የማይችል እንግት ፣ ባለቤቱን የማያስገባ ቤት ።

ራስ ሲመለጥ ፣ ነገር ሲያመልጥ ።

ራስ ሳይጠና ፣ ጉተና ።

ራስ ተላጭቶ ወለባ ፣ ልባልባ ታጥቆ አዛባ ።

ራስ ተከናንቦ ፣ ሙርጥ ገልቦ ።

ራስ ከተመለጠ ፣ ነገር ካመለጠ ።

ራስ ከዋለ ለምድ አይገድም ።

ራስ ከዋለበት ፣ እግር ይሰበሰባል ።

ራስ የት ትሄዳለህ ? ካንተ ጋር ፣ ስንቅሳ ? አንተሳ ።

ራስ ያለ አንገት ፣ ዕድቅ ያለ እውነት ።

ራስ ይሸብታል እንጂ ልብ አይሸብትም ።

ራቁቱን የተወለደ ልጅ ለምድ አነሰው ወይ ።

ራብ ይከላከላል ባቄላ ፣ ከጥፍ ያደርሳል ነጠላ ።

ራብ ይከላከላል ባቄላ ፣ ጥቃት ያወጣል ዲቃላ ።

ራብን ባለቤቱ ያውቀዋል ፣ ማን ይጠይቀዋል ።

ራብን ያማርራል ሰው ፣ ቁንጣንን ያልቀመሰው ።

ራት ቢንቁ አንድ እጅ ይለቃለቁ ፣ ዳኛ ቢንቁ ከመከራ ይወድቁ ።

ራት ቢንቁ ፣ አንድ እጅ ይለቃለቁ ፤ ዳኛ ቢንቁ ፣ የተያዘ እህል ይወቁ ።

ራት የለህም ቢሉት ፣ ከወጡ አውጡልኝ አለ ።

ራት የላት ፣ ምሳ አማራት ።

ራት ፣ የሰማይ መብራት ።

ራት የሌለው ቄስ ፡ ከልቡ አይቀድስ ።

ሬሳ በምን ከበደ ? ሃሳቡን በሰው ላይ ጥሎ ።

ሬሳ በዝምታው ይፈራል ።

ሬሳ ባልጋ ፡ ጥሬ በመንጋጋ ።

ርስት በሺ አመቱ ፡ ለባለቤቱ ።

ርስት ያጓግማል ፡ አቀበት ያደክማል ።

ርኅ መስሎሽ እርሾ ጥልቅ ።

ርጥብ ሬሳ ፡ ደረቁን አስነሳ ።

ርጥብ ከደረቅ ይነዳል ።

ሮሮ የማይመረው ፡ ኮሶ የማያሽረው የለም ።

ሮቃ የዝሆን አለቃ ፡ ለምሳር አይበቃ ።

## - ሰ -

ሰላላ መላላ ።

ሰላም ሰላም ለቅኔ ስራቂ ናሁዳ ፡ ዳር ዳሩን ኮርመም መሃሉን ሳይጎዳ ።

ሰላም ሰው በርበሬ አይሰርቅም ።

ሰሚ ልብ ነው ፡ ጆሮማ ቅጠል ነው ።

ሰማሁት ያሻማል ፡ አየሁት ያመሳክራል ።

ሰማህ ? አልሰማሁም ፡ አይህ ? አላየሁም ።

ሰማንያ ለማገጃ ፡ ስለት ለማረጃ ።

ሰማንያ አንድ መፅሀፍ ከተማረው ፡ መከራ የመከረው ይሻላል ።

ሰማይ ምን ይርቅ ፡ መንገደኛ ምን ይጨነቅ ።

ሰማይ ቢያኩ ፥ ጤፍ ቢሰኩ ።

ሰማይ ብልጭ ፥ ወፍ ጭጭ ።

ሰማይ አገሬ ፥ ምድር ወንበሬ ።

ሰማይ ከነግሡ ፥ ምድር ከነልብሱ ።

ሰማይ ይወድቃል ብላ ፥ ምሰሶ ይዛ ቆመች ።

ሰማይን ያህል ዳቦ ባገኝሁ ቢለው ፥ ኮከብን ያህል በላተኛ ያዝብሃል አለው ።

ሰምቶ መቻል ፥ ለእግዚአብሔር ይመቻል ።

ሰምቶ ዝም ፥ አይቶ ዝም ፥ በሆድ ያለ አይነቅዝም ።

ሰምና ወርቅ ፥ እንጀራና መረቅ ።

ሰርቆ ከማሰብ ፥ እጅን መሰብሰብ ።

ሰርቆ የጉም ሌባ ፥ ጉም ሲለቅ የት ሊገባ ።

ሰርገኛ መጣ ፥ በርበሬ ቀንጥሱ ።

ሰርገኛ ሳይመጣ ፥ ሙሽሪት ትመጣ ።

ሰርገኞች መጡ ፥ ብቅል አስጡ ።

ሰባት አመት የታወረ እውር ነገ አይንህ ይበራልሃል ቢሉት፥ዛሬ እንደምን አድሬ አለ።

ሰባት ወልዶ አቃቢትነት ።

ሰባት ጊዜ እንዴት ዋላችሁ አንዱ ለነገር ነው ።

ሰነፍ ሰው ያሰንፋል ።

ሰነፍ ሴት ፥ እድል የላትም ለንብረት ።

ሰነፍ ሴት ያገባ ፥ በሬው በሰኔ ገደል የገባ ።

ሰነፍ በአል ያበዛል ።

ሰነፍ ቢመክሩት ፥ ውሃ ቢወቅጡት ።

ሰነፍ እረኛ ከሩቅ ይመልሳል ።

ሰነፍ ይፀድቃል ቢለው ፣ ገለባ ይበቅላል ወይ አለው ።

ሰነፍ ገበሬ በመስከረም ያርማል ።

ሰናፍጭ ትቀምሽ ፣ ተልባ መስሎሽ ።

ሰኔ መቃጠሪያ ፣ ሀዳር መገናኛ ።

ሰኔ ፣ ነግ በኔ ።

ሰንበሌጥ ለቤት ፣ ቀሚስ ለባለቤት ።

ሰአሊ በስእሉ ፣ ፈጣሪ በፍጡሩ ።

ሰከሮ ከጌታ መገናኘት ፣ ከሹመት መለየት ።

ሰው ሆኖ አይስት ፣ እንጨት ሆኖ አይጨስ የለም ።

ሰው ሆኖ የማያስብ ፣ እንጨት ሆኖ የማይጨስ ።

ሰው ሆኖ የማይበድል ፣ እንጨት ሆኖ የማይጨስ ።

ሰው ለወደደው ፣ ዘንጋዳ ጤፉ ነው ።

ሰው ለወዳጁ ጫጩት ያርዳል ።

ሰው ላማኙ ፣ እግዚአብሔር ለለማኙ ።

ሰው መሳይ በሸንጎ ።

ሰው መታፈሩ ፣ በከንፈሩ ፤ መሬት መከበሩ ፣ በድንበሩ ።

ሰው መኖሩ ለመከበር ፣ የመሬት ወሰኑ ድንበር ።

ሰው ማመን ቀብሮ ነው ።

ሰው ማመን ገደለኝ ፣ የኔ እየመሰለኝ ።

ሰው ማማት ፣ የሰው ስጋ መብላት ።

ሰው ማን ያህላል ? የተናገረውን ።

ሰው ማጅራቱ አይታየውም ።

ሰው ምን በሰራ ፣ መቅረቱ ይወራ ።

ሰው ምን ቢዋሽ ፣ እግዜርን አያታልልም ።

ሰው ምን ይመስላል ? ቢለው ፣ ኑሮውን ።

ሰው ሲሄድ ላገር ፣ ንብ ሲሄድ ላጥር ።

ሰው ሲያረጅ ከርስቱ ፣ ባል ሲያረጅ ከሚስቱ ።

ሰው ሳይቸግረው ከሰው ቤት ይሄዳል ።

ሰው ቁመቱን አይቶ ደጃፉን ይሰራል ።

ሰው በሰው የተጠጋ ፣ ሰው ወጋ ።

ሰው በእህል እህል በዝርዝር ያምራል ።

ሰው በወሬ ፣ ዱቄት በሙሬ ።

ሰው በወደደው ይደግፋል ።

ሰው በዋለበት ፣ ውሃ በወረደበት ።

ሰው በዘመድ ፣ ከብት በገመድ ።

ሰው በዱር ፣ አይኑ ዝንጉርጉር ።

ሰው ቢሰባ ለመሬት ፣ አያህ ቢሰባ ላራዊት ።

ሰው ቢታጣ ፣ ተመለመለ ጎባጣ ።

ሰው ባላወቀው ይፈርዳል ፣ እግዜር ባወቀው ይቀጣል ።

ሰው ባገሩ ሰው ነው ።

ሰው ባገሩ ፣ ቤት በበሩ ።

ሰው ባገሩ ፣ አንበሳ በዱሩ ፣ አዞ በባህሩ ።

ሰው ባገሩ ወይራ ነው ።

ሰው አለቀ ፥ ምድር ተደባለቀ ።

ሰው አለብልሃቱ ገደል መግባቱ ፥ አለ ጉልበቱ ውሃ መግባቱ ።

ሰው አለወንዙ ፥ ብዙ ነው መዘዙ ።

ሰው አላሳቡ ፥ የሰው በቅሎ መሳቡ ።

ሰው አላገሩ ፥ ምነው መኖሩ ።

ሰው አላገር ፥ መሬት አለዘር ።

ሰው አትመኑ ፥ አብደል ዘመኑ ።

ሰው አየ ፥ እግዜር አየ ።

ሰው አይወድም በደል ፥ ከብት አይወድም ገደል ።

ሰው እሚበላ ቡዳ ፥ እጉድጓድ ሆኖ ይጠብቃል ።

ሰው እንደቤቱ እንጂ ፥ እንደ ጎረቤቱ አይበላም ።

ሰው እንዳቅሙ ፥ እህል እንደ ቀርሙ ።

ሰው እንዳነጋገሩ ፥ በቅሎ እንዳሰጋገሩ ።

ሰው እንግዳ ቢሆን ፥ እግዜር ባላገር ነው ።

ሰው ከመለመን ፥ አምላክን ማመን ።

ሰው ከመከረው ፥ መከራ የመከረው ።

ሰው ከሞተ የለ ንስሃ ፥ ከፈሰሰ አይታፈስ ውሃ ።

ሰው ከራበው የሰይፉን ሰገባ ይበላል ።

ሰው ከተከተተ ፥ ጅብ ከኮተኮተ

ሰው ከቆየ መዛመድ ፥ አህያን በገመድ ።

ሰው ከኖረ ከሚስቱ ይወልዳል ።

ሰው ካለሀል ፥ ምን ያሀል ።

ሰው ካለቤቱ ፣ ልፋት በከንቱ ።

ሰው ካላማ ፣ ጀንበር አይጠልቅም ።

ሰው ካልሞተና ካልሄደ አይመሰገንም ።

ሰው ወጣኒ ፣ እግዜር ፈፃሚ ።

ሰው የተጠጋ ፣ ሰው ወጋ ።

ሰው ያለበት አገር ፣ ሰው የሌለበት ዱር ።

ሰው ያለቤቱ ፣ ያንሳል ጉልበቱ ።

ሰው ያመነ ፣ ውሃ የዘገነ ።

ሰው ያስገድላል አባይ ፣ ውሃ ያስጮሃል ድንጋይ ።

ሰው ይለፋል ፣ እድል ይሰራል ።

ሰው ይውደድህ ፣ ድንጋይ ይጫንህ ።

ሰው ይጨርሳል እንጂ ሃሳብ አያልቅም ።

ሰው ይጨነቃል ፣ እግዜር ያውቃል ።

ሰው ጠባቂና ፆም ገዳፊ አንድ ነው ።

ሰውነቱን ቢንቁ ፣ ልብሱን ይጠይቁ ።

ሰውና አመሉ ሳይተዋወቁ ይኖራሉ ።

ሰውን ሰው አማው ፣ የራሱን ባይሰማው ።

ሰውን ሰው የሚያደርገው ፣ የራሱ ምግባር ነው ።

ሰውን እጎዳ ባይ ፣ አመድ ተንከባላይ ።

ሰውን ካልናቁ ፣ አጥሩን አይነቀንቁ ።

ሰውን ውደደው እንጂ አትመነው ።

ሰውዬው ውሃ ሲወስደው ፣ እኔም ወደ ቆላ ወርዳለሁ ብዬ ነበር አለ ።

ሰይጣን ለወዳጁ ድርብ ነው ።

ሰይጣን ቢያረምም ባህታዊ ይመስላል ።

ሰዶ ማሳደድ ቢያምርህ ፤ ዶሮህን ለቆቅ ለውጥ ።

ሰዶ ከማሳደድ የያዙትን ማጥበቅ ።

ሰጥቶ በእጅ ፤ መለመን ከሰው ደጅ ።

ሱሪ በአንገት አውልቁ ።

ሲሉ ሰምታ ፤ ዶሮ ሞተች ከጢስ ገብታ ።

ሲል ነበር ፤ ደግሞ ከወግ ይጨመር ።

ሲመሽ ወደ ቤቴ ፤ ሳረጅ ወደርስቴ ።

ሲመትሩለት ይነጭ ።

ሲመች ያማት ተስካር ይወጣል ፤ ሳይመች ያባት ይቀራል ።

ሲመክሩት ለማይሰማ ፤ ሲያበሉት ለሚከሳ ፤ ለዚያም ምክር ፤ ለዚያም እህል ንሳ ።

ሲመክሩት አይመከር ፤ በደም ይነከር ።

ሲመክሩት ያጠፋል ልጅ ፤ ሲያጥቡት ያድፋል እጅ ።

ሲመክሩት ይረሳል ፤ ሲከድኑት ይፈሳል ።

ሲምር ፤ ያስተምር ።

ሲሞላ ይፈሳል ፤ ሲከር ይበጠሳል ።

ሲሞቱ ቢያይ ያንቀላፋል ።

ሲሞቱ ገመድ ፤ ሲገዙ ዘመድ አይታጣም

ሲርበኝ ታነቅሁ ፤ ሲጨንቀኝ ታረቅሁ ።

ሲሮጡ የታጠቁት ፤ ሲሮጡ ይፈታል ።

ሲሮጥ የመጣ እህያን አጥብቀህ ጫነው ።

ሲሰሩ ሎሌ መስሎ ፡ ሲበሉ ጌታ መስሎ ።

ሲሰርቅ ያየሁትን ፡ ቢሰጠኝ አላምነውም ።

ሲሰበር ይሰንጠር ፡ ሲረዝም ይጠር ።

ሲሳይ በርምጃ ይገባል ፡ በሩጫ ይወጣል ።

ሲሳይ ያለቀበት አንበጣ ፡ ከድንጋይ ላይ ያርፋል ።

ሲስሟት ቀርቶ ፡ ሲስቧት ።

ሲሻሩ ከሳሽ ፡ ሲሞቱ ወራሽ አይታጣም ።

ሲሻኝ ፡ ጢስ ወጋኝ ።

ሲቀላውጡ አይን አፍጦ ፡ ሲቆፍሩ አንፈራጦ ።

ሲበሉ መደንደን ፡ ሲያጡ መቅጠን ።

ሲበሉ የላኩት ።

ሲበሉ የላኩት ፡ ሲናገር ያሳስታል ።

ሲበዛ ማር ይመራል ።

ሲበዛ ይገነፍላል ።

ሲበደሉ ማሩኝታ ፡ ቢበድሉ ይቅርታ ።

ሲታጠቡ ከክንድ ፡ ሲታረቁ ከሆድ ።

ሲናገሩት ያልሰማ ፡ ሲመቱት ያልደማ ።

ሲኖሩ ለጠቅ ፡ ሲሄዱ መንጠቅ ።

ሲወለድ ያጠለቀው ፡ ሲሞት አወለቀው ።

ሲወልዱ አየሁ ብላ በጠጧን ማለች ።

ሲወርዱ ፡ ይዋረዱ ።

ሲወጣ ባቱን ፡ ሲገባ ደረቱን ።

ሲዋጥ በመረቅ ።

ሲዞሩ በመኖር ዕድቅ ፤ ሲሙኙ በመኖር ወርቅ አይገኝም

ሲዞር ውሎ ፤ እራቱ ጥሬ ።

ሲያልቅ አያምር ።

ሲያምረኝ ፤ ይቅርብኝ ።

ሲያምኑት የከዳ ፤ አለበት እዳ ።

ሲያረጁ ፤ አንባር ይዋጁ ።

ሲያብል የተኛ ፤ ሲጠሩት አይሰማም ።

ሲያወላውል ፤ ቀረ ባጉል ።

ሲያውቁ በድፍረት ፤ ሳያውቁ በስህተት ።

ሲያውቅ የተኛ ፤ ሲጠሩት አይሰማም ።

ሲያውቅ ያሚገት ዳኛ ።

ሲያውቅ ያጠፋ ሰይጣን ።

ሲያዩት የማያምር ፤ ሲበሉት ያቅር ።

ሲያይ የገባን ፤ ሲሰማ ቅበረው ።

ሲያድጡት ይጥላል ።

ሲያዝሉት ይነክስ ፤ ሲያወርዱት ያለቅስ ።

ሲያጌጡ ፤ ይመላለጡ ።

ሲያጎርሱት የማያጎርስ ከቀማኛ አንድ ነው ።

ሲያጡ እጅ ላፍ ይጠናል ።

ሲገዙ ፤ ይገዙ ።

ሲጠላ ፤ ይጠና ።

ሲጠሩት አቤት ፣ ሲልኩት ወዴት ።

ሲጠሩት የቀረ ፣ ለምኖ ይሄዳል ።

ሲጠባ ያደገ ጥጃ ፣ ቢይዙት ያጓራል ።

ሲፈሩ አይከሱ ፣ በጉጣ አያርሱ ።

ሳለቅስ ሳነባ ፣ ስውል ሳሰማ ፣ የሰጠህኝ ሽማ ፣ ከደጅህ ተቀማ ።

ሳላውቀው እኔ ፣ ስንት ያመጣ ሰኔ ።

ሳል ያለበት ጎልማሳ ፣ ዘንጋዳ ያለበት ዳጉሳ አይጠቅምም ።

ሳል ይዞ ስርቆት ፣ ቂም ይዞ ፀሎት ።

ሳማና አለብላቢት ፣ ውሽማና ሚስት ።

ሳር ማጨድ በማጭድ ፣ ቤት መምረግ በጭቃ በጭድ ።

ሳር ይሸከሟል ለበሬ ፣ ቆንጆ ያገቧል ለወሬ ።

ሳቃዳው ፈሰሰ ።

ሳቢውን ገረፈው ።

ሳብል ብስቀው ፣ የምር መሰለው ።

ሳታት በግርግርታ ፣ ዳዊት በቀስታ ።

ሳታድፊ ፣ አትራፊ ።

ሳትታመም ተፈወስ ፣ ሳትረክስ ተቀደስ ።

ሳትዋጋ ንገስ ቢሉት ፣ ግድ ተዋግቼ እለ ።

ሳንባ ለድመት ፣ ገለባ ለከብት ።

ሳንባ ፣ ፍየል ላሰባ ።

ሳያረዱ ፣ አይሰደዱ ።

ሳያርሱ ግርድ ፣ አለዳኛ ፍርድ ።

ሳያሰረግጡ ወሬ ፣ ሳይገሉ ጎፈሬ ።

ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል ያድራል ።

ሳያሽረው የበላ ኮሶኛ ፣ ሳይፈርድ የበላ ዳኛ ።

ሳያውቅ የተረተ ፣ ሳይዘራ ያመረተ ።

ሳያድጉ ማደግ ፣ ያዳግማል ።

ሳያገቡ ማርገዝ ፣ ሳያረጁ መፍዘዝ ።

ሳይሆን ለጉም ፣ ሳይሰበር ጠግን ።

ሳይለማ በደለማ ፣ ሳይቃጠል በቅጠል ።

ሳይለግሙ ፣ ያግሙ ።

ሳይማሩ መተርጎም ፣ ሳይበጡ ማገም ።

ሳይማሩ ማንበብ ፣ ሳይበሉ መጥገብ ።

ሳይረቱ አይሞቱ ፣ አለዳኛ አይሟገቱ ።

ሳይረቱ ፣ አይበረቱ ።

ሳይርቅ በቅርቡ ፣ ሳይደርቅ በርጥቡ ።

ሳይርበው የሚበላ ፣ ረሃብን አያውቅም ።

ሳይሰሙ ማውራት ፣ መዋረድ አለበት ።

ሳይሰሩ ማግኘት ፣ ሳይፀድቁ ገነት አይገኝም ።

ሳይቀሱ መምሬ ፣ ሳይጠምዱ ገበሬ ።

ሳይቃጠል ፣ በቅጠል ።

ሳይቆጥር የሰጠ ፣ ሰጭውም ሌባ ፣ ተቀባዩም ሌባ ።

ሳይቆጥር ያኖረ ሌባ ፣ ሳይቆጥር የተቀበለም ሌባ ።

ሳይበሉ ማግሳት ፣ ልከበር ብሎ መጓጓት ።

ሳይባርክ ያርዳል ፤ ሳይታየው ይፈርዳል ።

ሳይተርፋት አበደረች ፤ ሳትቀበል ሞተች ።

ሳይታለም የተፈታ ።

ሳይታደሉ አይገዙ ፤ ሳያልቡ አይወዙ ።

ሳይታገል ጣይ ፤ ሳይወጋ ገዳይ ።

ሳይታፈሩ መገላገል ፤ እብድ ያሰኛል ።

ሳይቸግር ፤ ጤፍ ብድር ።

ሳይነገር ይፈርዱታል ፤ ሳይፃፍ ያነቡታል ።

ሳይከካ ፤ ተቦካ ።

ሳይውሉ ያዋዋሉ ፤ ይሰብሩ ላይጠግኑ ።

ሳይውል ሳያድር ፤ የሰው ልጅ ብድር ።

ሳይዘሩ ማጨድ ፤ ሳይራመዱ መሄድ ።

ሳይደወል ቅዱስ ።

ሳይገድሉ ጎፈሬ ፤ ሳያረጋግጡ ወሬ ።

ሳይጠሩት አቤት ፤ ሳይልኩት ወዴት ።

ሳይጠሩት አቤት ባይ ፤ ሳይሰጡት ተቀባይ ።

ሳይጠሩት የመሰከረ ፤ ሳይጠጣ የሰከረ ።

ሳይጠሩት የመጣ ፤ ሳይጠግብ የወጣ ።

ሳይጠሩት ይመጣል ፤ ሳይዘሩት ይበቅላል ።

ሳይጠይቁ አያውቁ ።

ሳይጠጡ መስከር ፤ ሳይሞቱ መቃብር ።

ሳይጣሉት የተጣላ ፤ ሲርብ ያበላ (አይረሳም)

ሳይያሙ ይፀድቃሉ ፡ ሳይታመሙ ይጠየቃሉ ።

ሳይፈታ ሚስቱን ፡ ሳይረታ ከብቱን ።

ሴት ለቤት ፡ ወፍጮ ለዱቄት ።

ሴት ማገዶ ቢቸግራት ፡ ምሰሶ ትነቅላለች ።

ሴት በማጀት ፡ ወንድ በችሎት ።

ሴት በጳጳስ ፡ ኳደሬ በንጉስ ።

ሴት ታውቅ ፡ በወንድ ያልቅ ።

ሴት አማት የመረዘው ፡ ኮሶ ያንዘዘው ።

ሴት ከበዛ ፡ ጎመን ጠነዛ ።

ሴት ከወንድ ፡ እህል ከሆድ ።

ሴት ከጠላች ፡ በቅሎ ከበላች ፤ አመል አወጣች ።

ሴት ካልወለደች ቋንጣ አትጠብስም ።

ሴት ካልዋሸች ፡ ባልዋን ትወልዳለች ።

ሴት የላከው ሞት አይፈራም ።

ሴት የወደደ ፡ ገሃነም እሳት ወረደ ።

ሴት ያመነ ፡ ጉም የዘገነ ።

ሴት ያወጣው ጠብ አይበርድም ።

ሴት ይወዷል ፡ ማጀት ያንጎዳጉዷል ።

ሴት ጅብ ትፈራለች ፡ አጥር ትመዛለች ።

ሴትና ቄስ ፡ ቀስ ።

ሴትና ቤት አይታመንም ።

ሴትና አህያ በዱላ ።

ሴትና ዶሮ ሳያብድ አይውልም ።

ሴትና ዶሮ ዱር ሲሄዱ ፣ ቤታቸውን ይከዱ ።

ሴትና ፈረስ ፣ እንደ ኩሬ ውሃ እያደር ማነስ ።

ሴትና ፈረስ ፣ የሰጡትን ይቀምስ ።

ስለ ላቁ ፣ ውል አያውቁ ።

ስለ ከሰሱ ፣ አይፈወሱ ።

ስለ ጨሰ አይነድም ፣ ስለ ዳመነ አይዘንብም ።

ስለ ፍቅር ፣ በስመ አብ ይቅር አለ ሰይጣን ።

ስለት ይቆርጣል ፣ ምላስ ያስቀጣል ።

ስለት ድጉሱን ፣ ደባ ራሱን ።

ስልህ እንዳልልህ ፣ አላገኘህ ።

ስልቻ ፣ ለስጋ መከተቻ ።

ስልቻ አሳሪ ፣ እርቦ ሰፋሪ ።

ስልቻና አቁማዳ ፣ ቆራጣና ጎማዳ ።

ስልጡን እንግዳ ፣ ይውላል ከጓዳ ።

ስመሰክርልህ ስመሰክርልህ ዋልኩ ቢለው ፣ ስታዘብህ ስታዘብህ ዋልኩ አለው ።

ስሙ ለባለቤት ፣ ቤተሰብ ናኘበት ።

ስሙን ለሰው አወረሰው ።

ስሙን ጠርቶ ፣ ራሱን ቆርቶ ።

ስም እኩል ፣ ስራው ስንኩል ።

ስም ከመቃብር ላይ ፣ ልብስ ያምራል በሰው ላይ ።

ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ።

ስም ይወጣ ከቤት ፣ ይከተላል ጎረቤት ።

ስምንተኛ ሺ ፣ ሰው አበላሺ ።

ስሩን የጠላ ፣ ራሱን የጠላ ።

ስራ ለሰሪው ፣ እሾህ ላጣሪው ።

ስራ ለሰሪው ፣ ወሬ ላውሪው ።

ስራ ከመፍታት ፣ ልጅን ላፋታት ።

ስራ ያጣ ለማኝ ፣ አፍሶ ይለቅማል ።

ስራ ያጣ መነኩሴ ፣ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል ።

ስራ ያጣ ፣ሚስት ያወጣ ።

ስራ ያጣ ገበሬ በሰኔ ይሞታል ።

ስራ ያጣ ገንፎ ያላምጣል ።

ስራ ያጣ ጢስ ይሞቃል ።

ስሱ ሲበላ ይታነቃል ፣ ሃሰተኛ ባነጋገሩ ይታወቃል ።

ስሱ አንድ ያንቀው ፣ አንድ ይወድቀው ።

ስበላ ቢመሽብኝ ፣ ጭንቅር ይበልብኝ ።

ስብ ያርዱ ፣ ጉፋያ ይነዱ ።

ስታበይው ፣ በልተሽ ታይው ።

ስታበጀው ውላ ፣ ባተላ ።

ስታቦካ ውላ ፣ ባተላ ።

ስትግደረደሪ ፣ ጦምሽን እንዳታድሪ ።

ስንቁን የተቀማ ነጋዴ ፣ ዋግ የመታው ስንዴ ።

ስንቃችን ፡ በልባችን አለ አሞራ ።

ስንቅ ያለው ጦም አያድርም ፡ ዋስ ያለው አይታሰርም ።

ስንቅህን ባህያ ፡ አመልህን በጉያ ።

ስንቅና ማህሌት እንደ ያዥው ነው ።

ስንቅና አባይ እያደር ይቀላል ።

ስንዝርና ጋት ፡ አባትና እናት ።

ስንዴ ምን አልኩ ዘመዴ ፡ ምስር እስኪ ቀስር ፡ አተር እስኪ ተርትር ፡ ባቄላ አንተም እንደሌላ ።

ስንዴ ራቱ ፡ ወይራ እሳቱ ፡ ማለፊያ ሚስቱ ፡ ለምን ሰርግ ይሄዳል ፡ ሰርግ አለ በቤቱ።

ስንዴ በጭንቅ ፡ ባለጌ በጥብቅ ።

ስንፍ የዶባ ፡ ላም የጋለሞታ ።

ስደቡኝ ባይ እመንገድ ላይ ያራል ።

ስደተኛ ሲሰነብት ፡ ይሆናል ባላባት ።

ስደት ለወሬ ያመቻል ።

ስደት ከጨዋ ልጅ ፡ መንገድ ካገር ልጅ ።

ስድብ በልጅ ያምራል ።

ስድብሽና ስድቤ እኩል ነው ፡ ትርፉ ሰው መስማቱ ነው ።

ስጋ ለጥጋብ ፡ አጥንት ለትካዜ ።

ስጋ ሰጥተው ቢላዋ ነሱ ።

ስጋ ቀረ ፡ እዳ ቀረ ።

ስጋ ቀርቦለት አይኑ ወደ ፈረስ ።

ስጋ ቁጠር ቢሉት ፡ ጣፊያ አንድ አለ ።

ስጋ ከመሬት ወድቆ አፈር ሳይዝ አይነሳም ።

ስጋ ከስጋ ነው ።

ስጋ ያንገፈገፈው ፣ ቀይ በሬ ሲያይ ይሸሻል ።

ስጋው ያሳማ ፣ ከበላው የሰማው ገማ ።

ስጋዬን ላራዊት ፣ ነፍሴን ለገነት ።

ስጡኝ አለማለት ፣ ከወዳጅ መስንበት ።

ሶስቱን ቢጠጣቸው ፣ ሁለቱን ጣላቸው ።

ሶስት ጊዜ ለካ ፣ አንድ ጊዜ ቅደድ ።

ሶስት ጊዜ እንዴት አደራችሁ ፣ አንዱ ለነገር ነው ።

## - ሸ -

ሸማ ለብሶ ስልቻ ፣ በቅሎ ጭኖ ለብቻ ።

ሸማ ማዋስ ለባላገር ፣ በቅሎ ማዋስ ለወታደር ።

ሸማ በውሃ ፣ ሰው በንስሃ ።

ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል ።

ሸማኔ በመኑ ፣ ጠይብ በከሰሉ ።

ሸማኔ በድሩ ፣ ጠይብ በመንደሩ ።

ሸማን ጠምዞ ያሰጧል ፣ እህልን አላምጦ ይበሏል ።

ሸምበቆ በመርዘሙ አይሆንም ምሰሶ ።

ሸርሙጣ ስታረጅ ፣ አቃጣሪ ትሆናለች ።

ሸርሙጣን የወደደ ፣ ልብሱን ጥሎ አበደ ።

ሸኝ ቤት አይገባም ።

ሹመት ሲገኝ ዘመድ አይገድም ።

ሹመት ፡ ሺህ ሞት ።

ሹመት በተርታ ፡ ስጋ በገበታ ።

ሹመትና ቁመት ከልኩ አያልፍም ።

ሹም ለመን ፡ አዘዘ ።

ሹም ለሹም ያወርሳል ፡ ጉም ተራራ ያለብሳል ።

ሹም መክሰስ ፡ ወጀድ ማረስ አይችግርም ።

ሹም ሲቆጣ ማር ይዞ እደጁ ፡ ደስ ሲለው ማር ይዞ እደጁ ።

ሹም ቢሞት ቀባሪው ሃምሳ ፡ የሹም ልጅ ቢሞት መቶ ሃም ሳ ።

ሹምና ማር እያደር ይከብዳል ።

ሹምና የጋማ ከብት ፡ በጊዜ ይከተት ።

ሹምና ጥጥ እያደር ይከብዳል ።

ሺ በመከረ ፡ አንድ በወረወረ ።

ሺ ዝንብ መሶብ አይከፍትም ።

ሺህ ቢታለብ ፡ ያው በገሌ አለች ድመት ።

ሺህ ያጭሽ ፡ አንድ ያገባሽ ።

ሺያጭ ገዥ ሆኖ ይገምታል ።

ሻው ል ሲሞት ፡ ሺህ ይሙት ።

ሽል እንደሆን ይገፋል ፡ ቂጣም እንደሆን ይጠፋል ።

ሽመልና ዘንግ ፡ ቂልና በግ ።

ሽማግሌ ሳለ ምክር አይጠፋም ፡ ጎልማሳ ሳለ ሳም አይነዳም ።

ሽማግሌ ካለበት ፡ ነገር አይናቅበት ።

ሽማግሌ ካልሞተ ፣ ስንዴ ካልመረተ ።

ሽማግሌ ይገላግላል ፣ የተጠቃ አቤት ይላል ።

ሽማግሌና ስልቻ ሳይሞሉ አይቆሙም ።

ሽማግሌና ጅብ በላላበት ይገባል ።

ሽማግሌን ከምክር ከመለየት ፣ ከምግብ መለየት ።

ሽበት እኖር ብዬ መጥቻለሁ አለ ።

ሽታና ግማት ፣ ላልሰማ ማውራት ።

ሽንብራ ፣ መኖር በመከራ ።

ሽንኩርት አንድም በሉት ገማ ፣ ደገሙትም ገማ ።

ሽንኩርት የባህሪውን ይሸታል ።

ሾላ በድፍን ።

ሾተልን ወደ አፎት ፣ ቁጣን ወደ ትእግስት ።

## - ቀ -

ቀለም ሲበጠበጥ ፣ ብርእ ቅረፁልኝ ።

ቀሊል አማት ፣ ሲሶ በትር አላት ።

ቀላጅ ፣ የሰይጣን ወዳጅ ።

ቀልብ የሌለው ውሻ ፣ ጠዲቅ አምጡልኝ ይላል ።

ቀሙን ላይቀር ከነጫማቸው ።

ቀማኛና ሽፍታ ፣ ጭለማና ማታ ።

ቀርቀሬ ወርጂ ማር ስልስ ማር ልክፍል ።

ቀስ ፣ እንዳይደፈርስ ።

ቀስ ፤ እንዳይፈስ ።

ቀበሮ የበሬ ቆለጥ ይወድቅልኛል ብላ ስትከተል ዋለች ።

ቀበቶ ለማፈኛ ፤ ሰንሰለት ለማቆራኛ ።

ቀበኛ ማሰሪያውን በልቶ ያሳጥራል ።

ቀበኛ ከብት ፤ ዋጋውን ያደርስ ።

ቀባሪ ፤ በፈጣሪ ።

ቀብረው ሲመለሱ እግዜር ይማርዎ ።

ቀን ሰው መስሎ ፤ ማታ ጅራት አብቅሎ ።

ቀን ሲደርስ ፤ አምባ ይፈርስ ።

ቀን በበቅሎ ፤ ማታ በቆሎ ።

ቀን ቢረዝም ፤ ልብ ያደክም ።

ቀን ቢቆጥሩ ፤ ውሻ ቢጠሩ ፤ ደረሰ በግሩ ።

ቀን እስኪወጣ ያባቴ ገበሬ ያግባኝ ።

ቀን እንደ ተራዳ ፤ ሌት እንደ ግድግዳ ።

ቀን ከህዝብ ፤ ሌት ከጅብ ።

ቀን ከጣለው ፤ ሁሉ ይጥለው ።

ቀን ካለቀሙ ፤ ሌት አይቅሙ ።

ቀን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል ።

ቀን የጎደለበት ጠገራ አይጥ ይበላዋል ።

ቀንና ጨርቅ ፤ እንደምንም ያልቅ ።

ቀንና ጨርቅ ያልቃል ፤ ብልህ ያውቃል ።

ቀንበር ታርቆ ፤ ጣውንት ታርቆ ምን ይሆናል ።

ቀንዱ ሰማይ ጠቀስ ፥ ጭራው ምድር አበስ ።

ቀንድ ካላት ላም ጎዳ ትከፋለች ።

ቀንድ ገብቶ ጅራት አይቀርም ።

ቀይ መላሱ ፥ ጥቁር እራሱ ።

ቀድሞ ሰኞን አለመሆን ነው ።

ቀጥኘ ቢያዩኝ ፥ ጅማት ለመኑኝ ።

ቁልቢጥ የላት ፥ ቁና አማራት ።

ቁመህ ተከራከር ፥ ዙረህ ተመሳከር ።

ቁም እንዳላማ ፥ ቁርጥ እንደ ጫማ ።

ቁምነገረኛ መምሰል ፥ የተለመደ አመል ።

ቁራ ሲነጣ ፥ አህያ ቀንድ ያወጣ ።

ቁራ ፥ ስሙን ይጠራ ።

ቁርበት ምን ያንጓጓሃል ? ቢሉት ፥ ባያድለኝ ነው እንጂ ፥ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ አለ ።

ቁና ለመስፈሪያ ፥ ብርብራ ለማስከሪያ ።

ቁንጫ መሄድ ሳትማር መዝለል ትማራለች ።

ቁንጫ ሞኝ ናት ፤ ቀን ትበራለች ፤ ተለቃቅማ ታልቃለች ።

ቁጥቋጦም ሲያድግ ዛፍ ይሆናል ።

ቁጭትና መረቅ ለጊዜው ይጣፍጣል ።

ቂል ሲረግሙት ፥ የመረቁት ይመስለዋል ።

ቂል አይሙት ፥ እንዲያጫውት ።

ቂል ከጠገበበት አይወጣም ።

ቂል ያገኘው ፈሊጥ ፣ ውሻ የደፋው ሊጥ ።

ቂልን አንድ ጊዜ ስደበው ፣ ሲሰደብ ይኖራል ።

ቂም ይዞ ፀሎት ፣ ጭድ አዝሎ ወዘት ።

ቂምህን አትርሳ ፣ የወደቀን አንሳ ።

ቂጡ የቆሰለ ውሻ እንደልቡ አይጮህም ።

ቂጡን የተወጋ ውሻ እንደልቡ አይጮህም ።

ቂጥ ገልቦ ክንብንብ ።

ቂጥኛም ከወርዶ ይውላል ።

ቂፍ ቂፍ ያሰኘሽ እንደ ቄብ ዶሮ ፣ ለመከራ ላሳርሽ ኖሮ ።

ቃልህ ሳይዘጋ ፣ እግርህ ሳይዘረጋ ።

ቄሱም ዝም ፣ መፅሀፉም ዝም ።

ቄስ ለኑዛዜ ፣ ፍቅር ለሚዜ ።

ቄስ እበር ፣ አረመኔ ከማህበር ።

ቄስና ንብ እያዩ እሳት ይገባሉ ።

ቅል ባገሩ ድንጋይ ይሰብራል ።

ቅልና ድንጋይ ተማቶ ፣ ሎሌና ጌታ ተሟግቶ ።

ቅልወጥ አሳስቦ ይጥላል ዘመቻ ።

ቅመሙ የበዛበት ወጥ ፣ አይፋጅ አይኮመጥጥ ።

ቅማል በጥፍር ቢድጧት ፣ ራስ ደህና አለች ።

ቅማል ከአካላት ፣ ምስጢር ከቤት ።

ቅማል ውሃ ውረጂ ቢሏት ፣ ስንዳሰስ ለመቼ ልደርስ ፣ ቁንጫ ውሃ ውረጂ ቢሏት ፣ ስፈናጠር የሰው ዶሮ እሰብር አሉ ።

ቅምዝምዝ ወዲያ ፍየል ወዲህ

ቅርንጫፉ ፡ እንደ ዛፉ ።

ቅቤ መዛኝ ድርቅ ያወራል ።

ቅቤ ተነጥሮ ለመብላት ፡ ያባት የናት ።

ቅቤ ይፍሰስ ፡ ከገንፎ አይተርፍ ።

ቅናት ፡ ያደርሳል ከሞት ።

ቅናት ጥናት ፡ አይገኝም ከናት ካባት ።

ቅንቡርስ የት ትሄዳለህ ? መተማ ፤ ትደርሳለህ ? ልብማ ።

ቅንነት ፡ ለነፍስ መድሃኒት ።

ቆሎ ለዘር ፡ እንዶድ ለድግር አይሆንም ።

ቆሎን ቢቆረጥሙት እንጂ ቢያኙት አያልቅም ።

ቆማጣን ቆማጣ ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል ።

ቆዳ ሲወደድ ፡ በሬህን እረድ ።

ቋንጣና ባለሟል ሳያር አይቀርም ።

## - በ -

በሁለት በትር አይማቱ ፡ በሁለት ዳኛ አይሟገቱ ።

በሃምሌ ወጨፎ ፡ በሰኔ እርከፍከፎ ።

በሃምሌ ጤፍ ይዘሩ ፡ ቤት ይሰሩ ።

በሁዋላ የመጣ ፡ አይን አወጣ ።

በለምለም መላሴ ኮሸሽላ በላሁ አለች አህያ ።

በሉት አለቀ ፡ ፈጩት ደቀቀ ።

በላይ በላዩ ያጎርሳታል ፥ የበላችው ያገሳታል ።

በል በል ይላሉ ሲፈርዱ ፥ ጣል ጣል ይላሉ ሲያርዱ ።

በልብ አምኖ ፥ ባፍ መንኖ ።

በልተው ከጨረሱ ፥ ከመኝታ ይነሱ ።

በልቶ መጠጥ ያጣ ፥ ተበድሎ ፍርድ ያጣ ።

በልቶ የማይበርደው ፥ የሰው ነገር የማይከብደው አንድ ነው ።

በልቶ የከሳ ፥ የነገሩትን የረሳ ።

በልቼ እንደ እንስሳ ፥ ተኝቼ እንደሬሳ ።

በልጅ አመካኝቶ ፥ ይበሏል አንጉቶ ።

በልጅነት ወደ ገዳም ፥ በርጅና ወደ አለም ።

በመልካም አንገት እንቅርት ።

በመረጡት ዳኛ ቢረቱ ፥ በቆረጡት በትር ቢመቱ ፥ በማን ያጉመተምቱ ?

በመሰለው ይናገራል ፥ ከበላው ይበላል ።

በመስከረም የሚያብድ ፥ በሰኔ ሱሪውን ከፍ ከፍ ያደርጋል ።

በመስከረም ጤዛ ፥ እንኳን አባቴ ጥጃ አልገዛ ።

በመሸታ የተገዛ ጦር ፥ ቢወረውሩት ከድፍድፍ ።

በመዘንከው ሚዛን ፥ በሰፈርከው ላዳን ።

በሙቅ ውሃ የታጠበ ፥ በሰው ገንዘብ የቸረ ።

በሚያዝያ ጎመን የዘራ ፥ ከረምቱን ሁሉ በላ ።

በማር ላይ ወተት ፥ ሲረባም ሲሰባም ።

በማር አጠገብ ፥ ውሃ ጥገብ ።

በማታየው ፥ እጅህን አታድርሰው ።

በማያድሩበት ቤት ፣ አያምሻሹበት ።

በምን የተነሳ ፣ ይህ ሁሉ ጠባሳ ።

በምንቸት ጠላ ቃፈላ ፣ ከጎረቤት ትጣላ ።

በምድር መጠቅጠቅ ፣ በሰማይ መጠየቅ ።

በምድር አለም ፣ አለገንዘብ የለም ።

በምግባሩ ፣ አይታወቅ ማማሩ ።

በምጥ ባጣሽ ፣ በእንግዴ ልጅ አላጣሽ ።

በሞኝ ክንድ ፣ የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበት ።

በሞኝ ክምር ፣ ዝንጀሮ ልጅዋን ትድር ።

በረጅም ጦር ባይወጉበት ፤ ያስፈራሩበት ።

በሬ ሆይ ፣ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ ።

በሬ ሲያረጅ ከጥጃ ጋር ይውላል ።

በሬ በመቶ ፣ ያውስ የት ተገኝቶ ፤ ምድር በዶሮ ፣ ያውስ ማን ገብሮ ።

በሬ በጭብጦ ተገዛ ቢለው ፣ ያላቦካ ከወዴት ያገኛል አለው

በሬ ተሾካሽኮ ቀንበር ፣ ገበሬ ተቸካችኮ ከድንበር ።

በሬ አርዶ በስለት ፣ ከብት አርብቶ በበረት ።

በሬ እንኳ ለወገኑ በፈርስ ያጓራል ።

በሬ ከጎለበተ ፣ አሽከር ከሰነበተ ።

በሬ ካራጁ ይውላል ።

በሬ ወደ አገሩ ይስባል ።

በሬ ያርሳል ፣ ምርቱን አህያ ያፍሳል ።

በሬና ሴት ፣ ካገርህ መሬት ።

በሬና በሬ መከሩ ፣ ቀንበር ሰበሩ ።

በርቄ ፣ እሞታለሁ ታንቄ ።

በርበሬ በገዛ እጅ ገብቶ ይፋጃል ።

በርበሬና ሚጥሚጣ ፣ ስጋና ቋንጣ ።

በርቦ ያበድራል ፣ በቁና ይከፈላል ።

በርኖስ ሳይገዙ ካባ ።

በርጥብ አያቃጥሉ ፣ በሰማንያ አይቀጥሉ ።

በሰለ እንብላ ፣ በለገ እንዝራ ።

በሰማንያ የተረታ ፣ መሃል አገዳውን የተመታ ።

በሰማንያ ያለቀ ፣ በፀሃይ የደረቀ ።

በሰማኸው ተማከር ፣ በሳልከው ተመተር ።

በሰማይ የለም ዱር ፣ በቁስ የለም ግብር ።

በሰማይ የለም ፀፀት ፣ ባባት የለም ቅጣት ።

በሰበቡ ፣ መምሬ ተሳቡ ።

በሰባት አመታቸው እንዳይማሩ ፣ ሰባ አመት ይደናቆሩ ።

በሰኔ ዘርን ይዘሩ ፣ ቤትን ይሰሩ ።

በሰንበት ላይ ደብረ ዘይት ፤ በስጋ ላይ አሞት ።

በሰው ምድር ፣ ልጅዋን ትድር ።

በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት ።

በሰው ቂጣ ፣ እጅዋን ትቃጣ ።

በሰው ቡሃቃ አሚጦ አይጋገርም ።

በሰው አገር ፣ አለመናገር ።

በሰው ፊት አያብሉ ፣ ሲታይ አይከበልሉ ።

በሴት የበከረ ፣ ከእግዜር ተማከረ ።

በሴትና በውሃ የማይርስ የለም ።

በስርቆት ከመከበር ፣ ይሻላል ደህይቶ መኖር ።

በስተእርጅና ፣ ድቁና ።

በሽማግሌ የታረቀ ፣ በፀሃይ የደረቀ ።

በሽምብራውም ትል አለበት ።

በሽተኛ ፣ ያድርቅህ መጋኛ ።

በሽታውን የደበቀ መድሃኒት የለውም ።

በሽታውን የደበቀ ሬሳው ይዘልቃል ።

በቀን ብዛት እንቁላል በእግሩ ይሄዳል ።

በቀኝ ቁሜ እንደ ክርስቶስ ፣ በግራ ቆመህ እንደ ዲያቢሎስ ።

በቁርበትም ያሰጣ ፣ በደላጎም ያሰጣ ፣ እኩል ቀን ወጣ ።

በቂል ክምር ፣ ዝንጀሮ ይማታበታል ።

በቃል ያለ ይረሳል ፣ በመፅሃፍ ያለ ይወረሳል ።

በቄስ ተናዘዝ ፣ በዘመድ ተገነዝ ።

በቄስ ተናዛዥ ፣ በመነኩሴ ገናዥ ።

በቅሎ ማሰሪያዋን በጠሰች ፣ በራስዋ አሳጠረች ።

በቅሎ ሳይገዙ ኮርቻ ።

በቅሎ ሽንቷን አጠራ ብላ ሃፍረቷን አሳየች ።

በቅሎ በኮርቻ ፣ ስንቅ በስልቻ ።

በቅሎ አባትህ ማን? ቢሉት ፣ ፈረስ አጎቴ አለ ።

በቅሎ እንደ ገሪው ፣ ህዝብ እንደመሪው ።

በቅሎ እንደሰገሩት ፣ እውር እንደመሩት ።

በቅሎ እንዳሰጋገሩ ፣ ሎሌ እንዳስተዳደሩ ።

በቅሎ ከሸጠ ፣ የሸመጠጠ ።

በቅሎ ያለ ኮርቻ ፣ ለማኝ ያለ ስልቻ ።

በቅሎ ግዙ ግዙ ፣ አንድ ጨው ላያግዙ ።

በቅሎ ጭኖ መጭ መጭ ፣ ሚስት አግብቶ ምሳዬን አምጭ ።

በቅጥ የኖረ በቅጥ ያገኛል ።

በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው ።

በቆረጡት ብትር ቢመቱ ፣ ባወጡት ዳኛ ቢረቱ ፤ የእግዜር ግቡ ከብቱ ።

በቆብ ላይ አብርጣም ፣ በመስቀል ላይ ውኻም ፣

በቆፈሩት ጉድጓድ ይገቡበታል ።

በበላህ ገብር ፣ በሰማህ መስክር ።

በበርበሬ የተገዛ ፈረስ መደቆሻ አይዘልም ።

በበሽታው የተጎዳ ፣ በጥንስሱ የተቀዳ ።

በበትሩ እማይማታ ፣ በዘመዱ እማይረታ ።

በበዛብህ ጊዜ የደነቆረ ፣ በበዛብህ አምላክ ሲል ይኖራል ።

በበጋ ፣ እሞኝ ቤት ተንጋጋ ፤ በክረምት ፣ እቤትህ ተከተት ።

በቡሃ ላይ ቆረቆር ።

በቢላዋ ያርዷል ፣ በውል ይሟገቷል ።

በባዳ ቢቆጡ ፣ በጨለማ ቢያፈጡ ።

በቤተ ዘመድ ገናኾ ፣ በቄስ ተናዛኾ ።

በቤት ይለምዱታል ፤ በአደባባይ ይደግሙታል ።

በብርሃን ካለቀሙ ፤ በጨለማ አይቅሙ ።

በብዙ ከማረስ ፤ ከተቀላቢው ማሳነስ ።

በተለሙ ያርፏል ፤ በጀመሩ ይጨርሷል ።

በተለይ ንዳ ፤ በጠራ ቅዳ ።

በተረገዘ ባመት ፤ በተወለደ በለት ።

በተሳለ ያርዷል ፤ በታየ ይፈርዷል ።

በተሾመ ይከራከሩበታል ፤ በተሻረ ይመሰክሩበታል ።

በተተከለ ግንድ ፤ በተፈተለ ገመድ ።

በተናጋሪ ዘንድ ሰሚ ይደነቃል ።

በተወረሱበት ዘመናት ፤ አይረጠጡበት ።

በተጀመረው ነገር ፤ በተጣበቀው ማገር ።

በትር ለገና ፤ ነገር ለዋና ።

በትር ለገና ፤ ውሃ ለዋና ።

በትር ከጅህ ፤ እባብ ተማርህ ።

በትንሽ መን ገድ ፤ ንጉስም አይሄድ ።

በትንሽ ማረሻ ፤ ትልቅ እርሻ ።

በትንባሆ የገዙት ጦር ፤ ቢወረውሩት ጋያ ይወጋል ።

በትኩስ ስጋ ፤ በርጥብ ፍለጋ ።

በችኮላ ያፈቀሩት ፤ በችኮላ ተጣሉት ።

በናት ላይ ሞግዚት ፤ በራት ላይ ዳረጎት ።

በናትና በልጅ መካከል መርፌ ጠፋ ።

በንብ ጊዜ ዝንብ ይነከሳል ።

በንጉስ ሞት አይዘበት ፤ በዝሆን ሃሞት አይፈተፈት ።

በንጉስ ሰው አይፈርድ ፤ በውሃ ላይ እሳት አይነድ ።

በንጹህ እቃ ላይ ዝንብ የምትቀምሰው አታገኝም ።

በአጤ ይሙቱ የተከተረ ፤ በስለት የተመተረ ።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ።

በእውር ይጠቃቀሱበታል ፤ በደንቆሮ ይንሾካሾኩበታል ።

በእውር ጎዳና ፤ ብርቅ ነው አንድ አይና ።

በእወ ቀቱ የጎለመሰ ፤ ብቻውን ነገሰ ።

በእድሜህ እወቅበት ፤ ሰርተህ ክበርበት ።

በከብቱ የለገሰ ፤ በፈረሱ የገሰገሰ ።

በካሳ የከበረ ፤ ባጓት የሰከረ ።

በካብ ላይ ብሰራ እባቡ መከራ ፤ በዛፍ ላይ ብሰራ አሞራው መከራ ፤ በምድር ብሰራ እረኛው መከራ ፤ የት ውዬ የት ልደር አድር ብዬ አለች ወፍ ።

በክረምት ፤ በርኖስከን አታውል እቤት ።

በወለዱ የከሰሰ ፤ በከብቱ የለገሰ ።

በወር ልቅ ፤ ባመት ቀሚስ ጥልቅ ።

በወተት ላይ ውሃ መጠጣት ፤ ያበዛዋል ያነጣዋል ።

በወንድሜ ግንባር ደም አልይበት ።

በዋስ ያለ ክብት ፤ በጣት ያለ ቀለበት ።

በዋጋ ፤ ከናትህ ልጅ ተዋጋ ።

በውሌ ፤ ደጃዝማች ነው ባሌ

በውል ከሄደች በቅሎዬ ፣ ያለ ውል የተበላች ቆሎዬ ።

በውርርድ ላይ ውርርድ ፣ ከነብር ላይ ስግርድ ።

በውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም ።

በውሽማ ሞት ፊት አይነጭም ።

በውሽማዋ ዳኝነት ባሏን ሁለት ጊዜ ረታችው ።

በውድ ሽጥልኝ ፣ በሃቅ መዝንልኝ ።

በዘር የላኩ በዝርዝር ፣ በጠዋት የላኩ በቀትር ።

በዘጠና ፣ የለም ጤና ።

በዚህም አዳርህ ፣ ግብር አለብህ ።

በዝሆን አፍ ቅርፊት ።

በዝሆን ጆሮ ትንኝ ።

በዝምታ ፣ ይገኛል ከበሬታ ።

በዝንጋታ ፣ ብዙ ጊዜ ይረታ ።

በየቤቱ ያለ ጥንስስ ጋን ይፈነቅላል ።

በየእለቱ ፣ ይወርዳል መአቱ ።

በየወንዙ ሃሌ ።

በያዘው ብትር አይመታ ፣ በወንድምና ባንቱ አይረታ ።

በደል ዋና አዋታ ትኖራለች ።

በደረቅ አበሳ ርጥብ ይነዳል ።

በደረቅ ይበላ ፣ በእርጥብ ይከላ ።

በደንባሪ በቅሎ ፣ ቃጭል ተጨምሮ ።

በደግነቱ ፣ ተቆረጠ አንገቱ ።

በዳቦ ላይ ሙልሙል ።

በድህነት ላይ ስንፍና ፣ በቂጥኝ ላይ ቁምጥና ።

በድሎ ማኑኘታ ፣ ተበድሎ ይቅርታ ።

በድንገት ፣ አህያ ገባ ከጅብ ቤት ።

በዶሮ ፊንጢጣ ፣ በሽንብራ ቂጣ ።

በጅ አግብቶ ቁንጣን ።

በጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ አንድ ነው ።

በጅ ያገኘሽ አያጣሽ ፣ ያጣሽ አያገኝሽ ።

በጅብ ሆዳምነት ፣ በአህል ጣፋጭነት ሳይተዋወቁ ይኖራሉ ።

በገቡበት ፣ አያወጡበት ።

በገና ጨዋታ ፣ አይቆጡም ጌታ ።

በገዛ ራሱ እባብ ጠመጠመ ።

በገዛ አረሟ ፣ እባብ ይዛ ታስፈራራ ።

በገዛ ዳቦዬ ልብልቡን አጣሁት ።

በጋለሞታ ቤት ፣ ሁሉ ይጣላበት ።

በግ ባልበላሽ ትበይኝ አለ ጅብ ።

በግ ከበረረ ፣ ሞኝ ካመረረ ።

በግ የሌለው ቀበሮን አውሬ አይላትም ።

በጎ አማጭን መጠር ፣ ክፉ አማጭን በጠር ።

በጎዶሎ ቀን የገዛሁት ጋሻ ሳያስገድለኝ አይቀርም አለ ፈሪ ።

በጠላ ላይ ውተት ፣ የግዜር ቸርነት ።

በጠረጠሩ ፣ ጠጠር ይጥሉ ።

በጠራ ተሻገር ፣ በተሳለ ምተር ።

በጠይቆ እውቀት ፣ ይገኛል ክብረት ።

በጠገበሁ ጠብ የለም ።

በጣም ሃብታም ፣ በጣም ድሃም ።

በጣይ ቅቤ አያበሩበትም ።

በጥቂት በጥቂት ፣ ይሞላል ልቃቂት ።

በጥባጭ ካለ ጥሩ ማን ይጠጣል ።

በጦም ቆሎ ፣ በዳገት በቅሎ ፤ ቆሎው ይከካል ፣ በቅሎውም ይነካል ።

በጨለማ እየሄዱ ጅብን ነገረኛ ያደርጋሉ ።

በጨዋታ ያልረታ ፣ ታጥቆ ያልመታ ፣ ይናደዳል ወደ ማታ ።

በጨው ደንደስ ፣ በርበሬ ተወደሰ ።

በጫማ የሚሄድና በቃሪያ የሚበላ ሰውን አይጠብቅም ።

በጭቃ የተመራ ፣ በቅቤ የተሰራ ።

በፈረስ የፈለጉት በእግር ይገኛል ።

በፊት እወቁኝ ፣ በሁዋላ ደብቁኝ ።

በፊት የደረሰን ወፍ ይበላዋል ፣ በፊት የተናገረውን ሰው ይጠላዋል ።

በፋሲካ የተቀጠረች ገረድ ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስላታል ።

በፍርድ ከሄደች በቅሎዬ ፣ ያለፍርድ የተበላች ጭብጦዬ ።

ቡሉኮና ጋቢ ፣ አቢላምና አላቢ ።

ቡቃያ አይታጨድ ፣ አንበሳ አይጠመድ ።

ቡቃያው አንድ ማሳ ፣ አራሚው አምሳ ።

ቡናና ፍቅር በትኩሱ ነው ።

ቢርበኝ ሰረቅሁ ፣ ቢጨንቀኝ ታረቅሁ ።

ቢሰናከል መንገዱ ፣ ጣለኝ ከወንበዴ ።

ቢሰጡኝ እንዳ ፣ ቢነሱኝ እረዳ ።

ቢስ የቢስ ለት ፣ ከፉ የከፉ ለት ።

ቢቆጡት የማይፈራ ፣ ቢናገሩትም አይሰማ ።

ቢቆጡት ያልሰማ ፣ ቢመቱትም ያው ነው ።

ቢበላ ገት ፣ ቢኖር አመት ።

ቢበይኑለት ቀጠነኝ ፣ ቢፈርዱለት ይግባኝ ።

ቢተኙ ነገር ፣ ቢሄዱ አገር ፣ ቢቆፍሩ አፈር አይታጣም ።

ቢተኙ ነገር ያገኙ ፣ ቢነሱ ነገር ይረሱ ።

ቢነግሩሽ ትናገሪብኝ ፣ ቢያጥቡሽ ትሰክሪብኝ ።

ቢናገር የማያምር ፣ ቢቀመጥ አይከበር ።

ቢከማች ፣ እዳው ላንቺ ።

ቢከፍቱት ተልባ ።

ቢወዱኝ ብሎ ሞት ፣ ቢጠሉት ምን ሊመጣበት ።

ቢዋደዱ ጠም ገደፉ ፣ ቢጣሉ ተዋረፉ ።

ቢዘል ማጀት ፣ ቢወጋ ምንቸት ።

ቢያብዱም ቢሞቱም ፣ የአንዱን ነገር አያጫውቱም ።

ቢያብዱም ቢጨምቱም ፣ ያንዱን ነገር ላንዱ አያወጡም ።

ቢያንጋልሏት ጡት የላት ፣ ቢደፏት ቂጥ የላት ።

ቢያዝሉት ያለቅስ ፣ ቢስሙት ይነክስ ።

ቢያዩኝ እስቅ ፣ ባያዩኝ እሰርቅ ።

ቢጠረጥሩ ፡ ጠጠር ይጥሉ ።

ቢጠሩት ያልሰማ ቢጠቅሱት አያይም ።

ቢጠሩኝ አቤት ፡ ቢልኩኝ ወዴት ።

ቢጠናባት ጠናች ፡ የልጅዋን ባል ቀማች ።

ቢፈትጉት ይነጣል ፡ ቢመረምሩት ይወጣል ።

ቢፈጀኝ በማንካዬ ፡ ባይፈጀኝ በጄ ።

ባህር ዛፍ ከተከሉት ይፀድቃል ፡ ገንዘብ ካላኖሩት ያልቃል ።

ባህያ ቆዳ የተሰራ ቤት ፡ ይበታተናል ጅብ የጮኸለት ።

ባለማ ፍረዱኝ ፡ ባጠፋ ስደዱኝ ።

ባለርስት የርስቱን ያህል ይከበራል ።

ባለቁርጥ አትደንግጥ ፡ ባለ አንቀልባ አታማጥ ።

ባለቤቱን አፈቱ ማመስገን ከማማት እኩል ነው ።

ባለቤቱን ካልናቁ ፡ አጥሩን አይነቀንቁ ።

ባለቤቱን ካልናቁ ፡ ውሻውን አይመቱ ።

ባለቤት ሲያፍር እንግዳ ይጋብዛል ።

ባለቤት የወደደው አሞሌ በሬ ይለውጣል ።

ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዳ አይቀበለውም ።

ባለቤት ያከበረው አህያ በቅሎ ይለውጣል ።

ባለነገር ከቤት ፡ ጠበቃ ከችሎት ።

ባለኩል ፡ ያሰናክል ።

ባለካባ ከባለካባ ፡ ባለዳባ ከባለዳባ

ባለጌ ማማቱን ፡ ቆዳ መንኳኳቱን አይተውም ።

ባለጌ ሲሞት ሬሳውን በሽመል ።

ባለጌ ሲቀመጥ ቂጡን ገልቦ ነው ።

ባለጌ ሲወዱት ፣ ከልጅ እኩል አድርጉኝ ይላል ።

ባለጌ ቁም ነገሩን ዒልት ያደርገዋል ።

ባለጌ አፉን እንጂ እግሩን አያድጠውም ።

ባለጌ ከበቅሎ የወጣ እንደሆን ፣ ከሰማይ የደረሰ ይመስለዋል ።

ባለጌ ካወራው ፣ የሰው ልጅ የገመተው ።

ባለጌ የተመከረለት ፣ ቁንጫ የተጠረገለት ይብሳል ።

ባለጌ ያለበት ሸንጐ ፣ ዝንብ ያለበት እርጎ ።

ባለጌ ጀሮ ከለበሰ ፣ አዋሽ ከደፈረሰ ።

ባለጌና ቆቅ በራሱ ያወራ ።

ባለጌን ካሳደገ ፣ የገደለ ፀደቀ ።

ባለጌን ገንዘቡ አያኮራውም ።

ባለጠጋ ሲቀናጣ ፣ የድሃ ልጅ ይሞታል ።

ባለጠጋ በከብቱ ፣ ድሃ በጉልበቱ ።

ባላዋቂ ቤት ፣ እንግዳ ናኘበት ።

ባላደራ ፣ ጩሀ በተራራ ።

ባላገር ሆደ ገር ፣ ከፉ አይናገር ።

ባላገር የሚበላው ቢያጣ ፣ የሚከፍለው አጥቶ አያውቅም ።

ባላጋራ ያለው ፣ እንቅልፍ የለው ።

ባልበላ ጭሬ አላፈሰም ወይ አለ ዶሮ ።

ባልነቃ ሰንጥቆ ፣ ባልዳመነ ባርቆ ።

ባልነበር ፣ ይሻል ነበር ።

ባልና ሚስት ካንድ ባህር ይቀዳል ።

ባልና ሚስት ፣ ፍትህና መንግስት ።

ባልንጀራህ ሲበልጥህ ፣ ቁንጣን ይምለጥህ ።

ባልንጀራህ ሲታማ ፣ የኔ ብለህ ስማ ።

ባልንጀራው ቢያጠቃው ወደ ሚስቱ ሮጠ ።

ባልንጀራዬ ሲበልጠኝ ፣ ቁንጣን ይፍለጠኝ ።

ባልወልድልሽ ፣ ታከትሁልሽ ።

ባልዋጇት ጣት ፣ የዘንዶ ጉድጓድ ይለካበት ።

ባልጋ የሚለያይ ፣ በፍቅር ይራራቃል ።

ባልፈሱበት ቂጥ ፣ አያፍሩበት ።

ባልፈጩሽ በኖብሽ ፣ ባልነበርሽ በርቆብሽ ።

ባመጣኸው ዳኛ ፣ ትሆን እስረኛ ።

ባምሌ በነሃሴ ፣ ቀረችልኝ ነፍሴ ።

ባሩዱ በከምሱር ይነሳል ፣ አንበሳ በዱር ያገሳል ።

ባስር ጣቱ ፣ በሰፌው ደረቱ ።

ባስተጋባ ፣ ከባህር ሄዶ ገባ ።

ባቄላ ሳይሰበር ፣ መነኩሴ ሳይቀበር ።

ባቄላ አለቀ ቢለው ፣ ፈስ ቀለለ ።

ባትዋጋ እንኳን ትሰለፍ ።

ባንዱ ታዘብ ፣ ባንዱ ተለዘብ ።

ባንድ ሁለት ፣ በጥሬ ዱቄት ።

ባንድ ራስ ፥ ሁለት መላስ ።

ባንድ አልጋ ፥ ሁለት አራስ ።

ባንድ አይን ጉድፍ ።

ባንድ አጉራ ፥ ሁለት አውራ ።

ባንድ አፍ ተናጋሪ ፥ ባንድ በቅሎ ሰጋሪ ።

ባንድ ከፈጩ የለም እመቤት ።

ባንድ ዙፋን ሁለት ንጉስ ።

ባንድ ደብር ፥ ሁለት መምህር ።

ባእድ ስር የለወ ም ።

ባእድ ከሳመው ፥ ዘመድ የነከሰው ።

ባዋቂ ፊት መናገር ፥ መታገም ።

ባይሰጡት ፥ ፈግጡት ።

ባይብ እንጂ በቅቤ አያወፍሩም ።

ባይቸኩል እንቁላል ይሄዳል በግሩ ።

ባይኔ መጣህብኝ ።

ባይኔ አልቅሼ ፥ በጄ አብሼ ።

ባዳና ጨለማ አንድ ነው ።

ባድላዊ ያድላበት ፥ ባመጠኛ ሰይፍ ይዘዝበት ።

ባግባቡ ፥ በደጃፉ ይግቡ ።

ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ ።

ባጡፋ ወታደር ፥ ይከሳል ባላገር ።

ባፈሳ ይታፈሳል ፥ በነጠር ይመለሳል ።

ባፌ ማን በላበት አለ እርኩም ።

ባፍ ይጠፉ ፣ በለፈለፉ ።

ቤተ ሰሪ በኋላ ይመጣል ።

ቤተክርስቲያን ለማላጅ ፣ ገበያ ላርፋጅ ።

ቤተ ክርስቲያን አቃጥል ቢሉት ፣ ደጇ ሰላም አቃጠለ ።

ቤተ ክርስቲያን የገባ ውሻ ።

ቤታቸውን እየከፈቱ ሰው ሌባ ይላሉ አለች ውሻ ።

ቤት ያለመወጫ ፣ ፊት ያለ አፍንጫ ፤ ያ መፈንጫ ፣ ያ ማጌጫ ።

ቤት ሲሰፋ ፣ የሰው ሁሉ ተስፋ ።

ቤት በማገር ፣ ንጉስ በባላገር ።

ቤት ቢሰፋ ፣ ደልሰ ተስፋ ።

ቤት አለ ክዳን ፣ ከምንም አያድን ።

ቤት ከነጉልላቱ ፣ ምድጃ ከነማዘንቱ ።

ቤት ዘግተው የደበደቡት ውሻ ባለቤቱን ይነክሳል ።

ቤት ያለ ሴት ፣ ከብት ያለበረት ።

ቤት ያለ ቁልፍ ፣ አልጋ ያለምንጣፍ ።

ቤት ያለ አጥር ፣ ሬሳ ያለ መቃብር ።

ቤት ያለ አጥር ፣ ሰው ያለ ልብስ ።

ቤትን መመስረት ፣ በባላገር እንጀት ።

ብላ ቢለኝ ፣ እንደ አባቴ በቆመጠኝ ።

ብልህ ያመቱን ፣ ሞኝ የለቱን ።

ብልህና ቅባት ፣ ብርሃንና መብራት ።

ብልህን ማሞኘት ፥ ቂምን ማቆየት ።

ብልጥ ለብልጥ ፥ አይን ብልጥጥ ።

ብልጥ ሰው ይታወቅበት አይመስለውም

ብልጥ አይን አስቀድሞ ያለቅሳል ።

ብልጥ አይጥ ከባለቤት እኩል ስትበላ ትኖራለች ።

ብሎ ብሎ ፥ የዶሮ አንገት ከማሰሮ ።

ብመታው ሰደበኝ ።

ብረት ለብረት ሲፋጭ ስለት ይወጣል ።

ብረት በብረት ይሰራል ፥ እውር በሰው ይመራል ።

ብረት ካልፈላ ፥ አይሳሳ ።

ብርሌ ከነቃ ፥ አይሆንም እቃ ።

ብርቅና ድንቅ ፥ ያለ አንድ ቀን አይደምቅ ።

ብርና ወርቅ ያምራሉ ፥ ግን ሰውን ያጣላሉ ።

ብርድ ቆላ ወረደ ፥ ልጅ አባቱን ወደደ ።

ብርድ ከማንቀጥቀጥ በቀር ምን ያመጣል ።

ብቅ ብቅ ፥ እንደ ስንዴ ምርቅ ።

ብቸኩል ያንቺንም የኔንም በላሁት ።

ብቻውን የሚሮጥ የሚቀድመው የለም ።

ብቻውን የሚሚገት የሚረታው የለም ።

ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል ።

ብነጨው ፈቴን ፥ ብመታው ደረቴን ።

ብንከባለል መንገዴ ፥ ጣለኝ ከወንበዴ ።

ብዙ ሃብት ፥ ያመጣል ብዙ ጠላት ።

ብዙ መሳም ፥ ልብ አይነካም ።

ብዙ ሰው ሊበላ ፥ አንድ ሰው ይጠላ ።

ብዙ ስንቅ የሚሸከም ሳይበላ ይወድቃል ።

ብዙ ቢተቹ ፥ ይሰለቹ ።

ብዙ ቢያወጉ ፥ ይዘንጉ ።

ብዙ ቧልት ፥ ያፈርሳል ንብረት ።

ብዙ እውር አየሁ ፥ እንዳንቺስ ፈረስ የለም ።

ብዙ ከብት ለማርባት ፥ አልቅትን ጠብቆ ውሃ ማጠጣት ።

ብዙዎች ለብዙ ሲያውቁ ፥ የራሳቸውን አይጠነቀቁ ።

ብጤ ከብጤው ።

ብጥለው ገለበጠኝ ።

ቧልትና ቅዘን ቤት ያጠፋል ።

ቧልተኛ ሰው አንቱ ሳይባል ያረጃል ።

## - ተ -

ተሁለት ዛፍ የወደቀ ።

ተሁሉም ያው ወንድም ፥ ቢከፋም ቢበጅም ።

ተለማማጭ ፥ አልማጭ ።

ተለማበት የተጋባበት ።

ተለጣጭ ፥ የጎረቤቷን ድልህ ሟጣጭ ።

ተላም የዋለ በሬ ፥ ተሴት የዋለ ገበሬ ።